ESQUQRE Adv.

ወርሀዊ Monthly
ሚያዝያ 2011

ቀንዲል Digital MAGAZINE

ቅፅ-1 ቁጥር-3

"......ለኔ
የምኖረውም
የማውቀውም
ኢትዮጲያዊነት
እሱ ነው!...."

ነፃነት ዘነበ (ሂፕኖቴራፒስት)

KENDIL 3rd Edition April 2019 | Digital Magazine

#ቅምሻ

ብቸኝነት ለሚወዱ ሰዎች አስደንጋጭ የጥናት ውጤት!

#ሀገሬ

" ሆ " ከማለት " ሀ " ማለት ይቀድማል!

#አብርሆት

" ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል" አለማንበብስ የሚያደርሰው ጉዳት አለ?

ማውጫ

3-4 ፠ ሀገሬ
" ሆ " ከማለት " ሀ " ማለት ይቀድማል!
(በሀይሉ ወንድይፍራው)

5-7 ፠ አብርሆት
" ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል " አለማንበብስ የሚያደርሰው ጉዳት አለ?
(በ ታምራት ታደሰ)

8 ፠ ትዝብት
ሞትን አለማመዳችሁን
(በ ዳዊት ላቀው)

9-13 ፠ የአውደብሩሀን ገፆች
ቆይታ ከ ነፃነት ዘነበ ጋር

14 ፠ ጥበባት
ጥቁር ምስል
(በ ሳኦል አክሊሉ)

15 ፠ ድሮና ዘንድሮ
ምስለ ሙሰሊኒያን
(በ ናሆም ሸዋንግዛው)

17-18 ፠ አጃኢብ
የትውልዳችን አዕምሮ ልሂቃን
(በ ያብስራ ካሳ)

19-20 ፠ አዕምሮ ጤና
ራስን ማወቅ
(በ ፍራኦል መስፍን)

21 ፠ ስነ-ፈለክ
(በ ኤርምያስ ደጀኔ)

23-24 ፠ ቅምሻ
ብቸኝነት ለሚወዱ ሰዎች አስደንጋጭ የጥናት ውጤት
(በ ዳዊት ላቀው)

26-27 ፠ እልፍ ገፆች
(በ ዮናስ ሀ/ማርቆስ)

28 ፠ ቴክኖሎጂ
(በ ዞስ ካለስ)

የአዘጋጁ መልዕክት

ሰላም ለእናንተ ይሁን!
የከበረ ሰላምታዬ በያላችሁበት ይድረሳችሁ።ለዛሬ መልዕክቴ መነሻ የሆነኝ ያለፉት አራት እና አምስት አመታት ያለን የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማችን እና አሁን አሁን ደግሞ ገደብ አልፎ ወደማጡ እያመራ እና እየመራን ያለ አስከፊ እና አሳሳቢ ጉዳይ ነው። በማህበራዊ ሚዲያዎች(በተለይ በፌስቡክ ፡በቴሌግራም፡በዩቲዩብ፡በ ኢንስታግራም እና በቲውተር) ሰብዓዊ ክብርን የሚገረስሱ እና ሆን ተብሎ የሚሰራጩ የጥላቻ ንግግር እና ሀሰተኛ መረጃ ስርጭት እጅጉን በዝተዋል። ይህ ደግሞ እንደ ሀገር ግጭትና ጉዳት ለእኩልነት ፡ ለሰላም፡ለ ዲሞክራሲ እና ለህዝቦች አንድነት ትልቅ ጠንቅ እየሆነ መሆኑን ለመረዳት የምርምር ወረቀት አያሻውም።

የጥላቻ ንግግር ምንድን ነው?

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጥላቻ ንግግርና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት ለመከላከል በወጣ አዋጅ ክፍል አንድ ቁጥር ሁለት ላይ የጥላቻ ንግግርን:- "የጥላቻ ንግግር ማለት የሌላን ግለሰብን፡ የተወሰነ ቡድንን ወይም ማህበረሰብን ብሄርን፡ ሀይማኖትን፡ቀለምን፡ጾታን፡ አካል ጉዳተኝነትን፡ ዜግነትን፡ ስደተኝነትን፡ቋንቋን፡ውጪያዊ ገጽታን፡ መሰረት በማድረግ ሆን ብሎ እኩይ አድርጎ የሚስል፡ የሚያንኳስስ፡ የሚያስፈራራ፡ መድሎ እንዲፈፀም፡ ወይም ጥቃት እንዲፈጸም የሚያነሳሳ ንግግር ነው።" በማለት ይገልፀዋል። አሁን ያለውን አጠቃቀማችንን በዚህ ሚዛን የመዘንን እንደሆን ግን እጅጉን አሳሳቢ እና ቀይ መስመር ያለፍንበት ሁኔታ ውስጥ እንዳለን እንገነዘባለን።

ሚዲያ በማህበራዊ ፡በፖለቲካዊ እና በኢኮኖሚያዊ ያለው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታው አስፈለጊ እንደሆነ ሁሉ በእውቀት፡ በሀላፊነትና በማስተዋል ካልተጠቀምንበት ደግሞ ጉዳቱ የትየለሌ ነው። የሩዋንዳው የዘር ጭፍጨፋ(በሬዲዮ በተላለፈ መልዕክት ነገሩ እንደከረረ ልብ ይበሉ!)፡ የአረቡ ሀገራት እና የሰሜን አፍሪካ ሀገራት ሌሎች ለዚህ እንደምሳሌ ማሳያዎች ናቸው።

ስለሆነም የሀገሬ ልጆች ለእምዬ ኢትዮጵያ ልናደርግላት ከምንችላቸው ብዙ ነገሮች መካከል የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማችን አንዱ እና ጊዜያዊው ዋነኛ አጀንዳ ነው። የሚለቀቁትን ፅሁፎች እውነተኛነት እና ሚዛናዊነት በማረጋገጥ፡ ጥቅምና ጉዳት በማመዛዘን፡ የውሸት እና የጥላቻ ነግግሮችን ባለመለጠፍ እና የተለጠፈውንም ለሰዎች ባለማጋራት ይሄን ተከትሎ ሊደርስ ከሚችል አስከፊ ችግር ሀገራችንን አስቀድመን መታደግ እንችላለን።

ለዚህም የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማችን በበሰለ እና በማስተዋል ይሁን! በማለት መልዕክቴን አበቃሁ። ሰላም!!

✍ኤርሚያስ ደጀኔ

ዋና-አዘጋጅ:- ኤርሚያስ ደጀኔ
✆0912178520
Email:-
ermiyasdejene@gmail.com
Telegram:- @Jeremy00

አዘጋጅ:- ሀና ሀይሉ
✆0935965345
Email:-
Hanahailu016@gmail.com
Telegram:- @HanaHailu

አርታኢ:- አወት ሀይለስላሴ
✆0920152581
E-mail:-
awoth12@gmail.com
Telegram:- @Awicha12

የመፅሔት ዲዛይን እና Editing:-
እስራኤል
✆0920019699
Email:- Esrumh1@gmail.com
Telegram:- @EsruMH

በሀይሉ ወንድይፍራው
(መባ ጥቁር ሰው)

ሆ ከማለት ሀ ማለት ይቀድማል

ስምሽ ከመዳቡ በጉልህ የተጻፈ
ሀገሬ ሀብት ነሽ ለ ዓለም የተረፈ
ዘር ሀረግ ቆጥሬ ፤
ከሰውነት ይልቅ ብሄር ካስመረጠኝ
በአፈርሽ ምላለሁ ፤
ያ ግርማ ሞገስሽ አንበሳው ይንከሰኝ።

ሆ ከማለት ሀ ማለት ይቀድማል .... “ሀ” የ ሀገር ገላጭ፣ የእውቀት አሀዱ፣ የመጀመሪያነት ምልክት “ሆ” ስሜትን እንጂ እውቀትን አይገልጽም። ዛሬ ላይ ሀገረዊ ስሜት ትተን በዘር እና በጎሳ “ሆ” እያልን ትናንት አባቶቻችን በክብር የገነቧትን ሀገር መሰረቷን ለመናድ እንደ ወጣት ከ እውቀት ይልቅ በስሜት፣ ከሀገር ፍቅር ይልቅ በ ብሄር እየተቧደንን እርስ በርስ በመናከስ ብዙ መስራት የምንችልበትን ወርቅ ግዜ ለትንሽ ስሜት እና ታሪክ ተወቃሽ በሚደርገን ስህተት ውስጥ ስንሰምጥ እያየን ነው። ውድ የቀንዲል መጽሔት አንባብያን እንደምን ቆያችሁኝ መቼም በአሁኑ ወቅት ከምንሰማው እና ከምናየው ችግር የተነሳ ደህንነት መጠየቅ ዋናው ጉዳይ ሆኗል ለዛም ነው በዛሬው የሀገሬ አምድ “ ሆ “ ከማለት “ ሀ “ ማለት ይበልጣል በሚል ርዕስ በአሁኑ ሰዓት በመላው ሀገራችን የሚታየውን የወጣቶች ስሜታዊነት ለመቃኘት እና ለወደ ፊት ይበጀናል የምለውን ብሎም እኛ ወጣቶች ሀገራችንን እንዴት ከስሜት ነጽተን ከተጋረጠባት ፈተና ማዳን እንዳለብን ልጽፍ የወደድኩት።

በሀገራችን ታሪክ ከታላቅ ገድል ፣ ስልጣኔ፣ ዘመነ መሳፍንት ሽኩቻ እስከ 1960 የተማሪዎች አብዮት እንዲሁም ከ ቅርብ ግዜ ማስታወሻ 1997 ዓ.ም እና ከ 2006 ዓ.ም ጀምሮ በሀገራችን ከታዩት የወጣቶች የለውጥ ተቃውሞ ጀምሮ የወጣቶች ተሳትፎ እጅግ የላቀ እና የማይካድ ሀቅ ነው። ነገር ግን ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በአሁኑ ሰዓት በሀገራችን በሚታዩት የስሜት ተከታይነት፣ የጥላቻ ንግግር ዋነኛ መራመጃ እየሆኑ ያሉት ወጣቶች ናቸው። ትናት እናት እና አባቶቻችን ቋንቋ ሳይዛቸው ከአራቱም አቅጣጫ በህይወት ጉዟቸው ሲተዋወቁ ዘር እና ብሄር ሳይሆን ፍቅር እና ሀገር ነበር ያስተሳሰራቸው የኦሮሞ ወጣት ፈረሰኞች፣ የሲዳማ፣ የጉራጌ፣ የወላይታ፣ የአፋር፣ የሱማሌ፣ የሀረር፣ የጋምቤላ፣ የአማራ፣ የቤንሻንጉል ወጣቶች ለአደዋ ጦርነት ሲዘምቱ የትግራይ እንስቶች በቋንቋ ሳሆን በሀገር ፍቅር ሀ ብለው ያን ሁሉ ጦረኛ ሲመግቡ የነበረው ከ ግለሰብ ይልቅ ሀገርን ስለሚያስቀድሙ ነው።

እኛ የዚህ ዘመን ወጣቶች ግለሰቦች የተደላደለ ቤት እየኖሩ ለኪሳቸው እና ሆዳቸው መሙላት ተጨንቀው በሚፈጽፉት የውሸት ዲስኩር እና ታሪክ እየተመራን ሀ ብለን ሀገርን በእውነት እና በእውቀት ከማገልገል እና ዘብ ከመቆም ይልቅ ሆ ብለን ወጥተን በስሜት ነገ ላይ እያለቀስን የማንገነባውን ሀገር ዛሬ በስሜት እና በውሸት ለማፍረስ እንማስናለን። እስቲ ስንቶቻችን ነን የተሟላ የጤና እና የትምህርት አገልግሎት ያለን? መልሱ ቀላል ነው ማናችንም የለን ዛሬ ላይ ተነስተን ወደ ሰሜን ብንሄድ ዛሬም ድረስ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለው በዳስ ውስጥ የሚማሩ ብዙ ናቸው፣ ዛሬም ድረስ በሳንካ የታመመ ወገናቸውን ይዘው ህክምና የሚያስሱ ብዙ ናቸው፣ ንጹህ ውሀ አጥተው ከ እንሰሳት እዳሪ ጋር እየተጋፉ የሚጠጡ በሁሉም ክልል አሉ፣ እየተራቡ ክፍል ውስጥ ቁጭ ብለው ስለ ሚበሉት የሚያስቡ እልፍ ናቸው።

ይህ ሁሉ ችግር ታቅፈን የኔ ብሄር ብቻ ትልቅ፣ የኔ ብሄር ብቻ ቀዳሚ፣ የኔ ብሄር ክብር ፣ ከተማረ ስለሌላው ምን አገባኝ በሚሉ ያልበሰሉ ሀሳቦች በብዙ እሳት ተፈትና በበሰለች ሀገር ላይ በስሜት ሆ ብለን ስናራምድ ልናፍር ይገባል። እስቲ ትናት አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለን ከፍ ሲልም ዩኒቨርስቲ ገብተን ማንነታችን ሰውነት ብቻ መሆኑን አውቀን በፍቅር የተጫወትናቸው ጠዋታዎች እኮ ለአንድነታችን ምስክር ናቸው፣ አንድ የዩኒቨርስቲ ዶርም ውስጥ ከሰሜን፣ ከደቡብ፤ ከምስራቅ እና ከምዕራብ የሀገራችን ክፍል ተሰባስበን ከቦንጋ የመጣው ማሩን በፍቅር ሲያካፍለን፣ ከደበብ የመጣው ጭቆ ሲያጎርሰን፣ ከሰሜን የመጣው በሶ ሲያጋራን ያኔ ለምን የኔ ብሄር፣ ዘር የሰራው ስላልሆነ አልበላም አልጠጣም አላልንም? ምክንያቱም ሀ ብለን ሀገር ሀ ብለን እውነት ሀ ብለን እውቀት እንጂ እንደ አሁኑ ዘመን አመጣሽ የዘር በሽታ ሆ ብለን ብሄር ሆ ብለን ዘር ሆ ብለን ስሜት አንከተልም ነበር። እየመረረንም ቢሆን መዋጥ ያለብን ሀቅ እኛ የሰው ዘር ነን ከ አንድ አፈር የተሰራን የአንድ አፈር አፈሮች ነን ላንለያይ የተሳሰርን፣ ላንበጠስ የተገመድን፣ ላንፈርስ የተገነባን የታላቆች ምድር የአቢሲንያ ልጆች ነን።

ለዛሬው የሀገሬ አምድ እንደማሳረጊያ ይሆነኝ ዘንድ ለሁሉም ኢትዮጲያዊ “ ሀ “ ብለን ሀገር ሳናስቀድም “ ሆ “ ብለን በስሜት ዘር እና ብሄር በሚል ከመኖሪያ ቀያቸው ተፈናቅለው ችግር ላይ ላሉ የጌዲዮ ወገኖች ድጋፍ እንድናደርግ ጥሪ አቀርባለሁ በተለይም ወጣቶች በስሜት ጭፈራ ያፈረስነውን በሀገራዊ አንድነት መገንባት ይገባናል።

የጌዴኦ እንባ

ጌዴኦ ከአመታት በፊት ቁጭ ብልን ጎረቤት እየጠራን በአንድነት ያፈላነውን ቡና ወገባቸውን አስረው ለቅመው እና አስውበው ሲያቀርቡ ዘመን አለፉ፣ ከለምለም ስፍራ ቅጭ ብለው የፍቅር ወግ ያወጉ ኮረዶች ዛሬ እርሀብ እና መከራ እየገረፋቸው ነው፣ ክፉን ከደግ ያለዩ ምስኪን ህጻናት በርሀብ ሰቆቃ እንባቸው ደርቋል፣ እርሶ የሚያበላው አባት እና ከማጀቷ ገበታ የማይጠፋት እናት ዛሬ ቁራሽ አተዋል፣ ፈደል መቁጠር የሚገባቸው በደል እየቆጠሩ ነው......ይህ ሁሉ እዚሁ ጠግቦ ምግብ ገንዳ ውስጥ የሚደፋባት ሀገር ላይ ሲሆን ህመሙ ይከብዳል። እኛ ክረምቱን በሞቀ ቤት ውስጥ ለማሳለፍ ስንጥር እስቲ ለደቂቃ እንኳ ብርድ እና ጸሀይ እየተፈራረቀ ህመም ለሆነባቸው፣ መሸሻ ለሌላቸው ለጌዴኦ እንድረስ እርሀብ ጊዜ አይሰጥም፣ ከምንጠጣው ውስኪ፣ ቢራ፣ ማኪያቶ እንኳ ቀንሰን ለነሱ አለሁ እንበላቸው፣ ስለ ወገብ እና ምሽት ጭፈራ የሚዘፍኑልን እስቲ ለተራቡ ይዝመቱልን።
ዛሬም ጌዴኦ ላይ ወገን እኛን ይጠብቃል...

ውድ አንባያን ከአደራ መልዕክቴ ጋር የዛሬውን አምድ በዚህ እየቋጨሁ በ ቀንዲል አራተኛ እትም በሌላ የሀገሬ ርዕስ እስከምንገናኝ እያንዳንዷ ቀን እና ሰዓት ለወገናችን አንድነት፣ፍቅር፣ስኬት የምንሰራበት እንዲሆን እየተመኘሁ በዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ ጥልቅ መልዕክት አዘል ግጥም ተሰናበትኩ።
አተላው ይደፋ!

የዘረኝነት ጉሽ ፣
......ያሰከረው ትውልድ ፤
አንጎሉ እንደዞረ ፤
አንጀቱ እንዳረረ ፤
..... ቀኑን ከሚገፋ ፤
ጋኑን አለቅልቆ ፣ አተላውን ይድፋ ።

‹‹ መልካም እና ሰላማዊ ሆነን ከተዋደድን በፍቅር የማይመለስ የለም ››
ኢትዮጲያ ለዘላለም በህዝቦቿ ፍቅር ትኑር...........

በታምራት ታደሰ ደነቀ
adissayer@gmail.com

"ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል" አለማንበብስ የሚያደርሰው ጉዳት አለ?

"No entertainment is so cheap as reading; nor any pleasure so lasting."
Lady M.W Montague

"ማንበብ ከመዝናኛዎች ሁሉ በዋጋው ርካሽ፣ ደስታዉ ደግሞ ለዘመናት የሚታወስ ነው።"
ሌዲ ኤም ደብሊው ሞንታጉ

ለመሆኑ የማያነቡ ሰዎች ምን ዓይነት ባህሪ ሊኖራቸው ይችላሉ ብለው ገምተውና አስበው ያውቃሉ ?

የማያነቡ ሰዎች የመሪነት ብቃታቸው እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው። መሪ ቢሆኑም በተሰጣቸው የሃላፊነት ቦታ ላይ ለውጥ ለመፍጠር ያላቸው ችሎታ ዝቅተኛ በመሆኑ ሰዎች እንዲረዷቸው ይፈልጋሉ የሰዎችን ሃሳብ ይከተላሉ እንጂ በውስጣቸው የራሳችን የሚሉት አዲስ ሃሳብ የለም። ቀናቸው በሙሉ ስለሰውና ሰለሚያዩት ክስተቶች ሲያወሩ ይዉላሉ፣ አዲስ ሃሳብ ከውስጣቸው አይፈልቅም፣ የፈጠራ ችሎታቸውም እጅግ ዝቅተኛ ነው። በህይወት የሚገጥማቸውን ችግር የመፍታት ብቃት ስለማይኖራቸው ስለ ግል ህይወታቸው ውሳኔ ሁልጊዜ የሌሎችን እገዛ ይፈልጋሉ፣ ለህይወታቸው ዕቅድ ስለሌላቸው ሌሎች የሚያደርጉት ትክክል ይመስላቸዋል ያንኑ በመኮረጅና በመድገም ይኖራሉ። ዓዕምሮአቸው አንድ ጉዳይ ብቻ ሲያወጣና ሲያወርድ ሥለሚውል ተፈጥሮ ያደላቸውን አቅምም ሆነ ዝንባሌ ባለማወቅ የቤቱ ቁልፍ እንደጠፋበት ፈዘው በመዞር ጊዜአቸውን ያጠፋሉ። ሃሳበ ግትር ከመሆናቸውም በላይ ነገሮችን በተለያዬ አቅጣጫ ማየት ማስተዋልና ማመዛዘን ስለማይችሉ ህይወት አማራጭ የሌላት አድርገው ያስባሉ። ሥራ የሚፈጠረው በአእምሮ ውስጥ ሲሆን እነደነዚህ ያሉ ሰዎች በተሰማሩበት የሥራ መስክ ኢንተርኔትና መብራት ከሌለ በእነርሱ አስተሳሰብ ሥራ የለም ሁለቱም ካለ ደግሞ በፌስቡክና በዩቲውብ በማይጠቅምና ለተቀጠሩበት ሥራ ተመጣጣኝ ባልሆነ ሁኔታ የሥራ ጊዜያቸውን በከንቱ ያጠፋሉ። ይህ ችግር ደግሞ በሥራ ቦታ ላይ በሰፊው ተንሰራፍቶ ይገኛል። በተጨማሪ የማያነብና በጥራት ትምህርተን ባልተማረ ህብረተሰብ ውሰጥ በጋራ ማሰብ፣ መውደድ፣ መጥላትና በደቦ መፍረድ የተለመደ ሲሆን ሥርዓተ አልበኝነትና ህገ ወጥነት ከመበራከቱም በላይ የህግ የበላይነትን በቀላሉ ለማስፈንና የሃገርን ሉአላዊነት ለማስጠበቅ አስቸጋሪ ይሆናል።

"A literate who doesn't carry on reading and a broken car are similar, both will never get anyone anywhere."
Tamirat T. DENEKE
"ተምሮ የማያነብና የተሰበረ መኪና ይመሳሰላሉ፤ ሁለቱም ማንንም የትም አያደርሱም።"
ታምራት ታደሰ ደነቀ

የማያነቡ ሰዎች አካባቢያቸውን ከማስተዋል፣ ከመመርመርና ከመለወጥ ይልቅ በሚበሉት፤ በሚለብሱት፤ በመጠለያና በሚያገኙት ገቢ ላይ ብቻ የአእምሮ ችሎታቸውን ሲያባክኑ ይኖራሉ። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ደግሞ በአብዛኛው ጊዜያቸው የሚጠፋው እገሌ ምን አለ፣ ምንስ ተባለ፣ ምንም ካላገኙ ደግሞ ወሬን በመፍጠር በውስጣቸው ያለውን ተስፋ አስቆራጭ አላማቢስ ስሜት በሌሎች ላይ በመዝራት እንዲሁም በማህበራዊ ገፅ ዛሬ ምን ተወራ በማለት በኢንተርነኔት ካፌ፣ በየግሮሰሪ ደጃፍ፣ በሻይ ቤትና ከተሌቪዥን ፊት ተቀምጦ ከወርቅና ዕንቁ የበለጠ ጊዜያቸውን በማባከን መዋል ነው። የማያነቡ ሰዎች የማዳመጥና የማስተዋል ችሎታቸው ዝቅተኛ ነው። ስለዚህ ጥበብና ማስተዋል ከእነርሱ እጅግ የራቀች ነች። ሰውን ይንቃሉ፣ ክቡር የሆነውን የሰው ልጅና ሕግን አያከበብሩም፣ ፈጣሪያቸውንም አያውቁትምና አይፈሩም። የማያነቡ ሰዎች በመጨረሻው ዘመን ለሃገርና ለትውልድ ትተውት ወይም ሠርተውት የሚያልፉት አንዳችም ነገር የለም። በማንበብ ዓእምሮአቸው ያልበሰሉ ሰዎች ከሌሎች ጋር የሚገጥማቸውን ችግር የሚፈቱት በረጋ አዕምሮና ማስተዋል ሳይሆን በመናናቅ በመጯጯህ ከሃላፊነት በመሸሽና ከዚያም አልፎ በመካሰስ በመጨረሻም በጦርነት ሊሆን ይችላል።

አእምሮአቸው በማንበብ ስላልበሰለ የመጠየቅና የመመርመር ችሎታቸው ዝቅተኛ በመሆኑ ተፈጥሮንና የፈጣሪን ጥበብ፣ ወደዚህ ምድር የመጡበትን ዓላማ ሳይረዱና ለማወቅም ጥረት ሳያደርጉ ወደማይቀረው የፍፃሜ ሞት ከሌሎች ጋር ተሰልፈው ለአንዴና ለመጨረሻ ወደ መቃብር ይወርዳሉ።

ያለማንበብ ከሚያደርሰው ጉዳት ለምሳሌ ያህል መጥቀስ ቢያስፈልግ አንዲት እናት ወይም አንድ አባት በዚህ ዘመን የተወለዱ ልጆቻቸውን የሚያሳድጉት እናትና አባታቸው ወይም አያት ባሳደጋቸው የልጆች አስተዳደግ ዘዴ ከሆነ በዘመኑ ልጆቸ እንደ ችግር ፈጣሪና ምንም እንደማያውቁ ተደርገው ይቆጠራሉ። ለዚህም ዋናው ምክንያት እናት ወይም አባት ምንም ዓይነት የማንበብ ዝንባሌም ሆነ ፍላጎት ቢኖራቸውም የማንበብ ባህሉ በጥልቀት ያልሰረፀ ከመሆኑም በላይ በኑሮ ጫናና በሌላም ሁኔታ እራሳቸውን ከማንበብ ጋር ለማቀራረብና በልጆች አስተዳደግ ወይም ልጆች የሚያልፍበትን የአካል፣ የሥነ ልቦና፣ የአእምሮ ዕድገት ለውጥንና ባህሪያቸውን ለመረዳት ዕድሉ ስለማይኖር በቀላሉ ለመግባባት ይቸገራሉ። በዚህም ምክንያት ወላጆች በልጆቻቸው ላይ በአእምሮ ብቃት የበላይነት ስለማይኖራቸው በዕድገታቸው ላይ የሚኖራቸው ተፅዕኖ እጅግ ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ በቤተሰብ ውስጥ የሚኖረው መግባባት ጥያቄ ውስጥ ይወድቃል።

ይህም ሁኔታ ለብዙ ቤተሰብ መፍረስና መበታተን፣ ለህፃናትና ልጆች መጎዳት፣ የተለያዬ ጥቃት መድረስ ምክንያት ሲሆን በአጭሩ ትውልድ አቅጣጫ እንዲያጣና ሃገር ደካማ እንድትሆን አስተዋፅኦ ያደርጋል። ይህ እንደምሳሌ ተጠቀሰ እንጂ አለማንበብ በሁሉም የሀገራችን ዙሪያ በሁሉም የሥራ መስክና የትምህርት ተቋማትን ጨምሮ እንደ ዋና ችግር ተንሰራፍቶ የሚገኝና ሊሰራበት የሚገባ ትልቅ ጉዳይ ነው። ስለዚህ የማንበብ ባህልን ለማስፋፋትና በማህበረሰቡ ያለውን የማንበብ ፍላጎት ለመጨመር እንዲሁም የወደፊት አንባቢዎችን ለመፍጠርና በሰፊው ለመድረስ እንዲቻል አለማንበብ የሚያደርሰውን ጉዳት በስፋትና በጥልቀት ለህብረተሰቡ ማስገንዘብ አማራጭ የሌለው መንገድ በመሆኑ ሁላችንም በሃላፊነት መሥራት አለብን። በተለይ የግልና የመንግሥት ትምህርት ተቋማት፣ የቤተ መፃሕፍት ባለሙያዎች፣ መምህራን፣ የተማረውና ማንበብን ባህሉ ያደረገው ምሁር ወ.ዘ.ተ የማንበብ ባህል በሃገራችን እንዲዳበር ያላሰለሰ ጥረት ማድረገ ይኖርበታል።

በማንበብ አዕምሮው የበሰለ ሰው ባህሪ ምንድነው?

“No matter what his rank or position may be, the lover of books is the richest and the happiest of the children of men.”
J.A. Langford
“በምንም የሃላፊነትና የሃብት ደረጃ ላይ ቢሆንም፡ መፅሓፍን ማንበብ ከሚወድ ሰው የበለጠ ደስተኛና ባለፀጋ የለም”
ጄ. ኤ. ላንግፎርድ

በማንበብ የታነፀ አዕምሮ ያለው ሰው የሚታወቀው በሚፅፋቸው ጽሑፎች፤ በሚያፈልቃቸው ሃሳቦች፤ ውስብስብ ችግሮችን በመፍታት ችሎታውና ሰፊ ትዕግስት ያለው እንዲሁም በማናቸውም ሁኔታ ለሚገጥሙት ችገሮች በማስተዋልና በመመርመር መፍትሄ መኖሩንና ነገም ሆነ ወደፊት አዲስ ሃሳብ ከአእምሮው እንደ ምንጭ ውሃ በማፍለቅ ለቸግሮች መፍትሄ መሰጠት የሚችል መሆኑን የሚረዳና በራሱ የሚተማመን፣ ጊዜውን ትርጉም ባለው ሁኔታ መጠቀም የሚችልና ዕውቀት ገደብ እንደሌለው በመረዳት እራሱን ዘወትር በማንበብ ማነፅ ማሳደግና ያላወቀውን ለማወቅ ጥረት የሚያደርግ ነው።

በማንበብ በትክክል ዓዕምሮውን ያዳበረ ሰው እራሱን ዝቅ ያደርጋል፤ ሌሎችን ከእርሱ ያነሱትን ይረዳል፤ በግል ህይወቱም ይሁን በሥነ-ምግባሩ እንዲሁም በተሰጠው የሥራ ሃላፊነት የተዋጣለት፣ ሰዎች እንደምሳሌ የሚጠቅሱትና የሚያከብሩት ሙሉ ሰው ይሆናል። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች በቀላሉ የሌላ ሰው የተዛባ ሃሳብና ዓላማ ማስፈፀሚያ ወይም መጠቀሚያ ሊሆኑ አይችሉም። የሚያነቡ ሰዎች የሰሙትን ሁሉ ይመረምራሉ ያመዛዝናሉ ውሳኔያቸውም ሚዛናዊነት ይኖረዋል። የሚያነቡ ሰዎች በአዕምሮ ፈጣን፣ የሌላውን ሃሳብ በቶሎ የሚረዱ ንቁና በአስተሳሰብ ጤናማ ሲሆኑ ረጂም ዕድሜም እንደሚኖሩ ይገመታል።

ታላቁ ፈላስፋ አሪስቶትል ስለሚያነቡና ስላማያነቡ (ስለተማሩና ስላልተማሩ) ሰዎች በአጭሩ እንደሚከተለው ገልፆታል። "በሚያነብና በማያነብ (በተማረና ባልተማረ) ሰው መካከል ያለው ልዩነት፣ በህይወት በሚኖርና በህይወት በማይኖር ሰው መካከል ያለውን ልዩነት ያክል ነው።" በአጭሩ አለማንበብ ከፍተኛ ጉዳት ሲኖረው ማንበብ ግን ይገራል፣ ዕውቀትን ያሰፋል፣ ጥበብን ያስተምራል፣ ከሥራ ፈቶች ይነጥላል፣ ከሃሳብ ያሳርፋል፣ ስኬትን ይጠቁማል፣ ድክመትን ያሳያል፣ ክብርን ይጠብቃል፣ ሰውን ሙሉ ያደርጋል ስለዚህ ማወቅ ያለብን ማንበብ ከዚያም በላይ መሆን እንደሚያስችል ነው። እዚህ ላይ ሳልጠቅሰው የማላልፈው ጉዳይ ቢኖር በማንበብ እጅግ ብዙ ጥቅም ማግኘት ሲቻል ይህ ካልሆነ ግን አንባቢው አንባቢ ለመባልና ባነበባቸው መፅሐፍት ውስጥ ባሉ ተዋናይ ሰዎች ህይወት (ባህሪያት) ውስጥ ሲዋኙቅና ሲቃኙ ቆይቶ የመጣ እንጂ ልምዳቸውን ከራሱ ህይወት ጋር፣ ከአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብና በማጣጣም ለራሱም ሆነ ለህብረተሰቡ ችግር መፍቻ ጥቅም ላይ ያላዋለ ሰው ስለሆነ ከማያነብ ሰው የተሻለ አይደለም።

በዳዊት ላቀው

ሞትን አለማመዳችሁን

የቀን ውሎዬ እንደ አብዛኛው ኢትዮጲያዊ የታክሲ ወረፋ በመያዝ ይጀምራል። ዛሬም እንደ አምናው ነው፤ የኑሮ ዘይቤ በርካታ የስነ-ልቦና ባለሙያዎች የሰው ልጅ የራሱን ህይወት ደራሲ አድረገው ይስሉታል። ለዚህም እንደ ማሳመኛ ነጥብ የሚያነሱት የበርካታ ስኬታማ ሰዎችን የጥረት ውጤት እና ስኬትን ነው። በእነርሱ አንድምታ ሰው ህይወቱን አዘቅት ውስጥም ከአዘቅትም የማውጣት እድሉ በ'ጁ ነው በማለት ነው ። ይህን ሀሳብ ባልቃረነውም ነገር ግን አዘቅት ውስጥ ባለች ሀገር ውሰጥስ? የህዝቦች መደማመጥ በሌለበት ሀገር ውሰጥስ? በተከፋፈለ ማህበረሰብ ውስጥስ? እላለሁ:: ለዚህም የህሊና ትዝብቴ መልስ የሚሰጡ የራሳቸውን ትንታኔ በመረጃ አስደግፈው ህዝብን የወቀሰውን ህሊናዬን ተሳስቷል ብለው ወደ ግለሰብ አውረደው አንተስ? በሚል ምፀት የሚያፋጥጡኝ አይጠፉም፤ይህን የሀሳብ ሙግት ይዤ ከቤቴ ወጥቼ ለአመታት በተመላለስኩበት መንገድ ጉዜዬን ቀጠልኩ። ጎዳናውን ይዤ በሁሳብ ሙግት ከህሊናዬ ጋር እየተሞገትኩ የጃቢርን ሱቅ አለፍኩት።

እዚ ሰፈር ከገባሁ ጀምሮ የማውቀው ባለሱቅ ነው የኔን እና የሱን ህይወት ስታዘበው ለውጥ አላይበት አልኩኝ። ዝም ብዬ ሳስበው ምናልባት ባለሱቁ በርካታ በር በባንክ ይኖረው ይሆናል ግን የሱቁ ቀለም ያዉ ነው ለውጥ አላየሁበትም፤ የሱቁ መጠን አልሰፋም፤ አልጠበበም፤ ያው ድሮ እንደማውቀው ነው። የባለ ሱቁ አለባበስ ያው ድሮ እንደማውቀው ነው ፤በሱቁ መስኮት ላይ ሆኖ ደንበኞቹን የሚጠብቅበት ሁኔታው ያው ድሮ እንደማወቀው ነው። ሱቁ እቃ ልገዛ ስሄድ በመንግስት ላይ ስለግብር መጨመር የሚያነሳው ምሬት የው ድሮ እንደማውቀው ነው ምንም ለውጥ አላየሁበትም። አትርፎ እንኳን ቢሆን በርካታ ሀብት ቢኖረውም ሀብቱ በህይወቱ ላይ ለውጥ ካላመጣ ያወ የዜሮ ድምር ነው። ያው እንደ ድሮው ያው... ያው....ያው ነው ያው!!!!!! ዝም ብዬ ሳስብ ብዙዎቻችን የቆመ አእምሮ ታቅፈን ነው የምንዘረዉ፤የቆመውን አእምሯችንን የሚነቃቃልን ሰው ያስፈልገናል። ብቻ እራሴንም ሌላውንም እየወቀስኩ ታክሲ ውስጥ ገባሁ። ታክሲ ውስጥ እንደ እድል ሆኖ ሰው ተጨናንቆ በሚቀመጥበት የመጨረሻ ወንበር ላይ እራሴን አገኘሁት።

ወደፊት ስመለከት በታክሲ ውሥጥ ያሉ በርካታ ጥቅሶች እና ተሳፈሪው ይታየኛል። ከጥቅሶቹ መካከል‹‹ አትስራና ስትዞር ውለህ አዞሩብኝ በል›› በዚህ ጥቅስ ውስጥ ብዙም መቆየት አልፈለኩም። አይኔን ወደ ተሳፋሪዎች ማማተር ጀመረኩኝ። ሁሉም በራሱ ሀሳብ ውስጥ ይነሆልላል። ታክሲው ልክ ሲነሳ ሬድዮውም አብሮ ተነሳ። "አድማጮቻችን ሁለት ሰአት ሁኗል ዜና እናሰማለን በቅድሚያም አርስተ ዜና" ብሎ አጎራ ከተሳፈሪው መካከል አንዳንዱ እጁ ላይ ያለውን ሰአት እየገረመመ አመሳከረ አንዳንዱም ሞባይሉን ከየኪሱ አውጥቶ ተገላመጠ:: ከመሸጋገሪያው ክላሲካል በኃላ አርእስተ ዜናው መነበብ ተጀመረ።
"በትላንትናው እለት በንትን ወረዳ ማንነቱ ባልታቀ ቡድን አስር ሰዎች ተገደሉ:" የሰቆቃ ዜና.... ሁሉንም ተመለከትኳቸው ማንም ምንም አለመሰለው:: እንደ ወትሮው ከንፈር የሚመጡ እናቶች እንኳ ዝምታን መርጠዋል።

ሁለተኛው ዜና ሲነበብ
"በትላንትናው እለት ከእንትን ወረዳ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ተፈናቀሉ፤ በርካቶችም ህይወታቸው አለፈ።" ማንም የገረመው ሰው አጣሁ። ሁሉም በዝመታ ነው፤ ደንገጥ ያለ እንኳ የለም። ሶስተኛው ዜና ቀጠለ....
"በትላንትናው እለት በንትን ከተማ በረካታ ሰዎች ለተቃዉሞ ወጥተው ከፀጥታ አካላት ጋር በተደረገ አለመግባበት በ10 ሰዎች ሞቱ፤በርካታ ህፃናት በደረሰባቸወ አደጋ ሆስፒታል መግባታቸው ታወቀ።"... አሁንም...ሁሉም ዝም!!... የሰቆቃው ዜና እንደቀጠለ ነው....ሌላ ሰቆቃ ...
እና ....
በታክሲ ውስጥ አብሬያቸው ከተሳፈሩኩት በተለያየ እድሜ ላይ ካሉ ሰዎች ጋር ትዝብቴን ጀመርኩ። እውነት ምንድነው የሰውን ነፍስ ከወፍ ነፍስ ያሳነሰው? ድሮ እንቅፋት ሲመታን "እኔን" ብሎ የሌላ ሰውን ሰቆቃ ለራሱ የሚመኝ በኔ ላይ ይሁን የሚለው ባህላችን የት ጠፋ? ማን አጠፋው? ማን ነጠቀን? በእናቶቻችን አንደበት ውሥጥ ያለው የሀዘኔታ ከንፈር መጠጣ የት ገባ? ማነው ሞትን ተራ አደርጎ ያለማመደን?!።

የዛሬው የአውደብሩሀን ገፆች እንግዳችን ነፃነት ዘነበ ይባላል። ነፃነትን የዛሬው እንግዳችን ስናደርግ በህይወታችን ላይ የሚጨምር ነገር እንዳለ እርግጠኛ ስለሆንን ነው። ሀሳባችሁን እና አስተያየታችሁን እንጠብቃለን።
መልካም ቆይታ!

<u>ቀንዲል</u>፡ በመጀመሪያ የዛሬው የቀንዲል መጽሄት የአውደ ብሩሀን ገጽ እንግዳችን በመሆንህ በቀንዲል መጽሄት ስም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በቅድሚያ እስቲ ወደ ጥያቄዎቼ ከመግባቴ በፊት ነፃነት ዘነበን ለአንባቢያን አስተዋውቅልን?

<u>ነፃነት</u> ፡ ጤና ይስጥልኝ እኔም እንግዳ አርጋችሁ ስለጋበዛችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ!
ነፃነት ዘነበ እባላለሁ። በመጀመሪያ በአካውንቲንግ ተመርቄ የተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ሰርቼያለሁ! ከዛ በኋላ ለረጅም ጊዜ ስለአይምሮ ማወቅ መማር ሰዎች የሚፈልጉትን ውጤት ማምጣት እንዲችሉ ከልቤ እመኝ ስለነበረ ካሊፎርኒያ በሚገኘው HMI ተምሬ ባሁን ሰአት ሂፕኖቴራፒስት ነኝ ማለት ነው!

<u>ቀንዲ</u>ል፡ እሺ አመሰግናለሁ ነፂ በቀጥታ ወደ ጥያቄዎቼ ልሂድና ሂፕኖቴራፒ ምንድነው? እንዴት ወደዚህ ስራ ልትገባ ቻልክ?

<u>ነፃነት</u>፡ወደ ሂፕኖቴራፒ ዋነኛው ምክንያት 1998 ዓ.ም ላይ አስር ከሚሆኑ ጓደኞቼ ጋር ራዕይ የሚል ስልጠና ወሰድኩ። እጅግ በጣም ውስጤ ተነክቶ እጅግ በጣም ውስጤ ተበጥብጦም ነበር። ስልጠናውን ስወስድ እንደዚህ አይነት እውቀት እንያለ እስካሁን እንዴት አላወኩም? በሚል ማለት ነው። ስለዚህ ከዛ ጊዜ ጀምሮ እነዚህን ነገሮች ላለማጣት ወሰንኩ እና ስለ ራዕይ ዲክሽነሪ ላይ አነበብኩ ትርጉሙ፡ምን እንደሆነ ከዚያ ደግሞ የተለያዩ personal development መፅሀፎች ላይ ምን እንደሚል ርዕሶቹን እያወጣሁ ማየት ጀመርኩ:: ከዛ የራሴን ራዕይ የመፈለጊያ ዘዴዎችን እዛ ላይ አገኘሁና መፈለግ ጀመርኩ:: አመት ከምናምን ፈጀብኝ በዛ ጊዜ ውስጥ በግልፅ የኔ ራዕይ "የተፈጠርኩበት የህይወቴ አላማ ማገልገል ያለብኝ ለሰዎች የሰዎችን ህይወት በአዎንታዊ መልኩ፡መቀየር ምሳሌ በመሆን" የሚል ነው! አዎንታዊ የሚለው ፍቅራቸው ላይ ሰላማቸው ላይ ጤናቸው ላይ ገቢያቸው ላይ ወዘተ… በጎ ዋጋቸው ላይ ከጨመሩ በጎ ለውጥ እለዋለሁ ማለት ነው እና. ..ስለዚህ ለዚህ አላማ ማንበብ ነበረብኝ መማር ነበረብኝ። ለውጥ ዋናው አመለካከት ላይ እንደሆነ በሂደት ስረዳ በዛ ባለሞያ መሆን እንዳለብኝ እየተገበዘብኩ መጣሁ:: ስልጠናዎችን በመስጠት ሲዲዎችን በመቅረፅ መፅሀፎችን በማሳተም አንድ ለአንድ በማስተማር በነዚህ በነዚህ እየሰራሁ ቆየሁና ስለሂፕኖ ቴራፒ መረጃውን ሳገኝ ደግሞ ሰዎች ቮኬሽናል ግባቸውን ለማሳካት ከሜዲካል እገዛ ውጪ ፕሮፌሽናል አማካሪ ይፈልጋሉ:: ስለዚህ እኔ ለገንዘብ የማልሰራው ግን ራዕዬን እንድኖር የምሰራው ብዬ ይሄን አዘጋጀሁ:: ተምሬ ጨረስኩ ለራሴ ተጠቀምኩ እውቀቱን እጅግ በጣም ተአምራዊ ለውጥ የሚያመጣ እውቀት ነው:: ስለዚህ ለሌሎችም እየሰራሁ እገኛለሁ ማለት ነው:: በነፃ ፍቃደኛ የሆኑ የቸገራቸው ለውጥ ማምጣት የሚፈልጉ ቴራፒው የሚያስፈልጉ ወንድም እና እህቶቼን ኢትዮጲያዊያንን በነፃ ለማገልገል ነው ወደዚህ ሙያ የመጣሁት!

<u>ቀንዲል</u> : በልጅነት ከዛም በመጀመሪያዎቹ የወጣትነት ጊዜህ እንዴት አይነት ሰው ነበርክ?
<u>ነፃነት</u>: በልጅነቴ እጅግ በጣም ፈሪ አይናፋር ሰዎች ሲሰበሰቡ የምፈራ አይነት ልጅ ነበርኩኝ። በትምህርቴ አለ አይደል ሀያ ቤት አስራምናምን ቤት ውስጥ ውጤት የሚያመጣ አይነት ልጅ ነበርኩ:: ስለዚህ ያን ያክል ጎበዝ የምባል አልነበርኩም:: ከሰው ጋርም መግባባት እጅግ ስለምፈራ ግን ጨዋታ በጣም ስለምወድ ቤት ውስጥ ከወንድሜ ጋር ከቅርብ ጓደኞቼ ጋር ደስ ብሎኝ የምጫወት ሰው ነበርኩ:: በወጣትነት ጊዜዬ ደግሞ በጣም ግብ ላይ ያተኮረ ህይወት ነበረኝ ደስታን እወዳለሁ: ግን የዛሬ አራት አመት ብዬ እስባለሁ::

ለምሳሌ ዘጠነኛ ክፍል ሆኜ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ማትሪክ ፈተና እያነበብኩ ምን ያክሉን አውቃለሁ ዘጠኝን ከጨረስኩ እኮ አንድ አራተኛውን ማወቅ አለብኝ ብዬ አልም ነበር:: አንድ ነገር ስጀምር መጨረሻውን አስቤ ነበር ማደርገው እንዴት ዴቨሎፕ እንዳረኩት እሱን አላውቅም። እእእ... በጣም መስጠት እወዳለሁ:: መስጠት ማለት ከጎደለኝ ላይ ካለኝ ላይ ብቻ! በተለይ ጊዜዬን ቀናነትን በጎ ነገር ለሰዎች ማድረግ እጅግ በጣም ያስደስተኛል:: ክፍት ባለበት ውስጤ ይታመማል የያዝኩትን ነገር በጣም በስርዓት እና በዲሲፕሊን ነበር የምይዘው:: ስለዚህ በእንደዚህ አይነት ነበር ወጣትነቴን ያሳለፍኩት።
እንደውም መጀመሪያ ንግድ ባንክ ነበር ተቀጥሬ የምሰራው እና ምን ይሉ ነበር "ኦ በቃ ነፃነት መቼም አይወጣም ነበር የሚሉት" ግን ደግሞ መስሪያ ቤት ቶሎ ቶሎ ነበር የምቀይረው ምክንያቱም ህይወቴን የሚለውጥ ነገር እፈልጋለሁ:: የያዝኩትም ነገር ሁሉ አክብሬ እሰራለሁ ጥዋት 30 ደቂቃና ከዛ በላይ ቀደም ብዬ ነው ስራ ቦታ የምገባው ሲያልቅም ወደ ቤት ለመሄድ ብዬ ሳይሆን ስራዬን ለመጨረስ ነው ምቸኩለው:: ያላለቀ ስራዬን ወደቤትም ቢሆን ይዤ ሄጄ እሰራለሁ እንጂ ጭንቅላቴ አያርፍም ነበር ወጣትነቴ ይህን ይመስል ነበር!

ቀንዲል : የህይወት መርሄ ይሄ ነው የምትለው ነገር ካለ ብታካፍለን?

ነፃነት :እሺ በህይወቴ ያለኝ መርህ በሂደት ተቀርፆ ተቀርፆ ተቀርፆ የተቀመጠው በ1993 ዓ.ም ትዝ ይለኛል.... የህይወቴ መርህ ብዬ 15 ነገሮች ፅፌ ነበር ከዛ በኋላ ተጠቃለው ከስኬት መርህ ጋር፡ተብላልተው በውስጤ በደንብ አድገው አሁን ድረስ እጅግ በጣም የምከተላቸው
1,በራዕይ በትልቅ ህልም በግብ መንቀሳቀስ እነሱን እየቀረፁ በነሱ ላይ መኖር።
2, በምንም ሁኔታ ውስጥ ብሆን ራዕዬን ህልሜን ግቤን ማመን።
ባጣም ማመን!ባገኝም ማመን!
ሰዎች ቢቀበሉትም ማመን! ባይቀበሉትም ማመን!
ቢከፋኝም ብደሰትም ማመን!
ስለዚህ በምንም ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ማመን!
3, መተግበር እና መፅናት።
ለአላማዬ የሚያስፈልገኝን ስነ ስርዓት እለት እለት በግቤ መሰረት መስራት እና በዚያ ውስጥ በፅናት መቀጠል አላማዬ ጋር እስክደርስ
4,ቀና አስተሳሰብን ማጎልበት።
ስለሰው : ስለራሴ : ስለጊዜ : ስለትላንት : ስለነገ : ስለሀገሬ : ስለቤተሰቤ : ስለስራዬ : ስለ ገቢ : ስለመንፈሳዊ ህይወቴ : ስለ አገልግሎት ወዘተ...
ስለነዚህ በጎ ነገሮችን ማሰብ:: ቀና ነገርን መናገር:: ቀና ነገርን መስራት:: የሚል ነው!! ስለዚህ ስወድቅ ያስተካክለኛል:: ከበጎ ትንሽ ብወጣም ተመልሼ በቀናነት እንድቀጥል ያደርገኛል።....

"... መስሪያ ቤት ቶሎ ቶሎ ነበር የምቀይረው ምክንያቱም ህይወቴን የሚለውጥ ነገር እፈልጋለሁ። ...."

..የመጨረሻው ምስጋናና ፀሎት ነው ።
ምስጋናና ፀሎት እጅግ በጣም ወሳኝ ነው ሁላችንም እናውቀዋለን ግን ከልብ በደስታ በፍቅር በምስጋና ስሜት ውስጥ ሆኖ የሚያደርጉት ጥቂቶች ናቸው።ብዙ ሰው እንደ አቴንዳስ ነገር ነው ፀሎትን እና ምስጋናን የሚያየው ነገር ግን ከዚያም በላይ ነው። የተሰጠን ብዙ ነገር አለ:: በዛ ጥልቅ ስሜት ውስጥ ሆኖ እነዛን ማመስገን በሀሳብ የተሰጠን አለተ በተግባር የተሰጠን አለ። በፈተና የተሰጡን ብዙ ናቸው እነዛን ስንከፍታቸው ስንፈታቸው እጅግ በጣም ትልልቅ ከፍታ በውስጣቸው አለ!
እነዚህ የህይወት መርሆቼ ናቸው።....

ቀንዲል : ስኬት ላንተ ምንድነው? በወጣትነት ዘመናችን ስኬትን እንዴት መጎናፀፍ እንችላለን?
ነፃነት : በወጣትነትም እድሜም ከዛ በኋላም በማንኛውም ጊዜ ማሳካት ይቻላል። መቼም ብዙ ሰዎች፡ለኔ ስኬት እያለ ያስቀምጣል እንጂ ቃል አንድ ነው። ትርጉሙ ብዙ ሰው አሁን አሁን መዝገበ ቃላትን አይጠቀምም ቃል ህይወት ከሆነ መዝገበ ቃላት ማለት መዝገበ ህይወት ማለት ነው!
ስለዚህ መዝገበ ቃላት ላይ ስኬት የሚለውን ቃል ፈልጎ ማግኘት ብሎ ይተረጉመዋል። ስለዚህ አንድ ሰው ለራሱ ለሌላውም ቢሆን ሌሎች ላይቀበሉት ይችላሉ። ግን በጎ የሆነን ነገር ፈልጎ ሲያገኝ ተሳካለት ይባላል። ፈልጎ ማግኘት ደግሞ ሁሌም፡ ይቻላል። ምክንያቱም ላመነ ሁሉ ስለሚቻለው ማለት ነው። ስለዚህ በየትኛውም ዘመን ሰው የፈለገውን ማግኘት ማሳካት ይችላል ምክንያቱም ሰው ያስባል እግዚአብሄር ይፈፅማል! እግዚአብሄር ከመፈፀም ወደ ኋላ አይልም! ምንም ይሁን የምናስበው የሚበጅ የማይበጅ ክፉም ይሁን በጎ ሀሳቡን በትክክል ካደረግነው እግዚአብሄር መፈፀሙን ሁሌ በታማኝነት ያደርጋል:: ስለዚህ ያቺን የማሰብ ሂደት ያለማወቅ ነው:: ብዙ ሰው ጋር ያለው እንዴት የሚለው እዛ ጋር ይፈታል እንዴት ማሰብ እንዳለብኝ ማወቅ ነው ፍላጎቴን ያ ደግሞ ቴክኒኮች አሉት ስልጠናዎች አሉት::

Under the power of believe የሚል ስልጠና አለ:: ዲዛይን አደረኩት እና ብዙ ሺ ሰዎችን አሰልጥኛለሁ። ባለፉት አስር አመታት ብዙ ሺ ሰዎች ውጤት አምተውበታል። ለማንኛውም አንድ ሰው በየቀኑ ከመተኛቱ በፊት የሚፈልገውን ነገር በስዕል ለጥፎ ለ15 ደቂቃ ቁጭ ብሎ ስዕሎቹን አይቶ አይኑን ጨፍኖ በህሊና ውስጥ ሲሳካለት የሚሰማውን ስሜት የሚኖረውን ሁኔታ እያሰበ በአይነ ህሊናው ቢያይ ብዙ ድግግሞሹ እምነት ያመጣለታል ሚስጥሩ እምነት ነው፡ ማለት ነው። እሱ ውጤት ይሰጣል ማለት ነው። በዛ መልኩ ስኬትን መጎናፀፍ ይቻላል::
ቀንዲል : በህይወቴ ፈተና ሆኖብኝ አልፌዋለሁ የምትለውን ጊዜ እስኪ አስታውሰን?
ነፃነት፡ በህይወቴ ፈተና ሆኖብኝ ያለፍኩት ነገር ወዲያው ጥያቄውን ስታነሺ ትዝ ያለኝ ቤቴል አካባቢ እኔና ባለቤቴ ተከራይተን እንኖር ነበር። ገና እንደተጋባን ለሶስት አመት 700 አካባቢ የቤት ኪራይ እንከፍል ነበር። የተቀጠርኩት ትቼ የግሌን ስራ ጀምሬ ነበር። የምሰራው ስራው በመሀል ችግር ገጠመው ስራዬን ለማሳደግ ጠንክሬ መስራት ነበረብኝ ባለቤቴ ደግሞ አራስ ሆናለች። ቤታችን ውስጥ የሚበላ የለንም። ከቤት ቦሌ ድረስ በእግሬ መሄድ ነበረብኝ ለ 6 ወር ያህል በእግሬ ወይ ግማሹን ወይ ሙሉውን ስመጣ ወይም ስሄድ በእግሬ ነበር የምሄደው። በጣም ከባድ ነበር። መንገድ ላይ እየሄድኩ ይደክመኛል ከዛ ሁለት ማንነቶች ያወራሉ አንደኛው አንተ ማትረባ ጓደኞችህ ባንክ ነው ያሉት ተቀጥረው እየሰሩ አሁን ማናጀር ሆነዋል እነሱ በመኪና አንተ በእግርህ ትሄዳለህ ይለኛል። ይኸውልህ ልጅህ የሚጠባው ወተት የለም : የጤፍ አጥሚት እየሰራህ : አንተን ብሎ አባት አንተን ብሎ ባል : ይለኛል። Almost literally ይሰድበኛል። ይርበኛል ሆዴ በዛ በኩል ይንጫጫል። ከዛ ፀሀይ ይመታኛል። ወዘተ.... ሌላው ማንነቴ ደግሞ no..no.. no ግድ የለም በዚህ መንገድ ብትሄድ ስኬታማ ትሆናለህ ቀጥል ...ዛሬ ወተት ላትሰጥ ትችላለህ፡ ለውዷ ባለቤትህ ምግብ ላታቀርብላት ትችላለህ፡ ግን ነገ በ5 ስታር ሆቴል፡ውስጥ ልትመግባቸው ትችላለህ! ብዙ ላሞችም ገዝተህ አንዷ ከነጭ አንዷ ከጥቁር እየታለበለት ሊቀርብለት ይችላል! ልክ ይሄኛው ጭንቅላቴ ሲያወራ ድካሜ ይጠፋል እንደዛ እየሄድኩ ደግሞ ነጌቲቭ ሀሳቤ ሲጨቀጭቀኝ እደክማለሁ:: ከዛ ከ6 ወር በኋል ገቢያችንም ተሻሻለ ብዙ በህይወታችን ትልልቅ ነገሮች አሳካን፡እና ሰው በተፈተነ ሰዓት በጎ ህሊናውን ይቻላል የሚለውን መንገድን ተስፋውን የሚያስበውን ህሊናውን እሱን ማሰብ ማመላለስ መቀበል ትልቅ ሚስጥር ነው።ብዙ ፈተና ቢኖርም ይቺኛዋ ታስተምራለች ብዬ ስላሰብኩ ነው::

ቀንዲል : ራዕይ/vision/ - ህልም/Dream/ - ግብ / Goal/ ምን ያህል ዋጋ እንዳለው ማወቅ ከፈለግሽ ነፃነትን ጠይቂው አሉኝ:: ብዙዎች በዚህ እንደምሳሌ ያነሱሀል እስቲ ልዩነታቸው ምንድነው? ለህይወታችን ምን ያህል ፋይዳ አለው?

ነፃነት : ራዕይ /visoion / ማለት የተፈጠርንበት ምክንያት ነው:: ለምሳሌ አልጋ የተፈጠረበት ምክንያት ሰው እንዲተኛበት ነው:: ላፕቶፕ ሰው የተለያዩ ስራዎችም እንዲሰራ ነው እያለ ይቀጥላል:: ሰውስ ለምን ተፈጠረ? አንዳንድ ሰው ዝም ብሎ በዘፈቀደ የተፈጠረ ይመስለዋል:: እንዲ ብሎ ማመን ትልቅ ኪሳራ ነው! ስለዚህ እኔማ ያለዓላማ አልተሰራሁም ፈጣሪዬ ትልቅ ነገር በውስጤ አስቀምጧል ያ የተቀመጠው ደግሞ ለደስታችን ነው። ስናደርገው ስንተገብረው ስናገለግለው ልብ አርጉ ማገልገል ነው! ራዕይ ስለዚህ ሳገለግለው ደስ የሚለኝ ገንዘብ ባገኝበትም ባላገኝበትም ደስ የሚለኝ ራዕይ ያባላል!
ህልም የምንለው ሰባት የህይወት ክፍሎችን በእያንዳንዱ ለራሳችን ብኖር ብለን የምናስበው
ለምሳሌ 1,ቤተሰብ ብለን፡ምን አይነት ቤት ውስጥ ፣ ምን አይነት ፣ማቴሪያሎችን ጨምሮ ብቻ ሳይሆን ጨምሮ
2,መንፈሳዊ ህይወት
ምን አይነት መንፈሳዊ ህይወት ውስጥ አገልግሎት ከፈጣሪዬ ጋር
በአመት በወር በሳምንት እለት እለት ምን አይነት ትስስር መስርቼ መኖር ነው ምፈልገው?
3,ገቢ
ለገቢ ምን አይነት ስራ እየሰራሁ እኖር ዘንድ እወዳለሁ?

4,ማህበራዊ ህይወት
በዙሪያዬ ካሉ ሰዎች ጋር፡ምን እየሰራሁ በምን አይነት ፍቅር ሰላም ጤና መኖር እፈልጋለሁ
5,ጤና ነው
ምን አይነት ተግባራትን ለጤናዬ መተግበር እፈልጋለሁ? ምን አይነት አቋም ይኑረኝ?
6,እውቀት
ምን አይነት እውቀት እፈልጋለሁ?በምን መልኩ እውቀቴን ላሳድግ?
7, አገልግሎት /ራዕይ
እንዴት ነው ማገለግለው? በምን መልኩ አገልግዬ ነው የሰዎችን ህይወት የምለውጠዉ?
ግብ ደግሞ ህልምን ለማሳካት የሚጠቅሙ የአጭር ጊዜ የመካከለኛ ጊዜ የረዥም ጊዜ የሚያልቁ የሚፈፀሙ ናቸው ማለት ነው!
መጀመሪያ ራዕይ ያስፈልገናል ህልሞቻችን ራዕያችንን የሚያስኖሩን ግቦቻችን ደግሞ ህልሞቻችንን የሚያሳኩ መሆን አለባቸው ማለት ነው::

ቀንዲል : ኢትዮጵያዊነትን እንዴት ትገልፀዋለህ?

ነፃነት : ኢትዮጲያዊነትን እንዴት ትገልፀዋለህ ስትዪ ለኔ ህሊናው ውስጥ ያለ ኢትዮጲያዊ አለ::
"ቀና :ሰው አክባሪ : እንግዳ እንዲመጣለት የሚለምን : ከዛም በናፍቆት የሚሸኝ :ዝቅ ብሎ እግር የሚያጥብ:ሰው የሚወድ :ደፋር :ጀግና: በሀገሩ በሚስቱ ሲመጡበት ህይወቱን የሚሰጥ :ከገንዘብ ይልቅ ዋጋ/value የሚያስቀድም ለዋጋው /value የሚሞት : ስነስርዓት ያለው ሰው" ለኔ ኢትዮጲያዊ ነው:: የሚገባኝ እሱ ነው! ከዛ ውጪ እየሆነ ስላለው ነገር ኢትዮጲያዊ ያልሆኑትን ነገር ኢትዮጲያ አልላቸውም ለኔ የምኖረውና የማውቀውም ኢትዮጲያዊነት እሱ ነው!

ቀንዲል: ነፂ ቀንህ እንዴት ተጀምሮ ያልፋል? በየቀኑ ከምታደርጋቸው ነገሮች ዋና ዋናዎቹ ምንድናቸው?

ነፃነት : ቀኔን ጥዋት ስጀምር በደንብ በመተኛት ስራ ከሌለኝ እስከ 3 ሰዓት እስከ 4 ብሎም እስከ ምሳ ሰዓት ልተኛ እችላለሁ::
ስራ ካለኝ ለሊት ልነሳ እቻላለሁ ማለት 11 ሰዓት ልነሳ እችላለሁ ስነሳ ግን መጀመሪያ ማስበው የቀን ግቤን ነው to do list ከአጀንዳዬ ወይም ከስልኬ አያለሁ::ከዛ ቀኔን አስተካክላለሁ:: እያንዳንዱ የምሰራው ነገር ከህልሞቼ ጋር ከግቦቼ ጋር የተገናኘ ነገር መሆን አለበት ከነዚህ ውጪ ብዙም ለማጥፋት ፈቃደኛ አይደለሁም::
ስለዚህ በቀን ውስጥ መፅሀፍ አነባለሁ ማሰለጥናቸውን ሰዎች ልጆች online choach አደርጋለሁ::
ከባለቤቴ ከሰብሊ ጋር እና ከልጆቼ ጋር ጥሩ ጊዜ አሳልፋለሁ አብሮ በመጫወት በመብላት ወይም ልጆቼን በማስጠናት ሊሆን ይችላል..
ከዛ የተወሰኑ ከpersonal development ጋር የተገናኘ ቪዲዮ ወይም audio አዳምጣለሁ::
ብዙ ሀላፊነቶች ስላሉብኝ እነሱን በትክክለኛው ጊዜ መጨረስ ስላሉብኝ እነሱን በትክክለኛው ጊዜ ለመጨረስ እሞክራለሁ:: ብዙ ጊዜ በማንበብ ወይም ስራዎቼን በመስራት እና ግቦቼ ላይ to do list በማውጣት በዋናነት ደግሞ visualise በማድረግ ድብቁን አይምሮ/ subconcious አይምሮዬን ፕሮግራም አደርጋለሁ::
ምስጋና ከመተኛቴ በፊት ሀምሳ ሀምሳ እፅፋለሁ ለተደረገልኝ እና ህልሞቼን እንደተደረጉ አድርጌ አመሰግናለሁ እጅግ በጣም ከፍታ ላይ ያለውስሜት እንዲሰማኝ ያደርጋል እነዚህን በዋናነት እሰራለሁ::

ቀንዲል : ወደ ግል ህይወትህ ልግባና ነፃነት ምን ያዝናናዋል? ምን ያስከፋዋል?

ነፃነት : ምን ያዝናናኛል? አብሮ ተሰብስቦ መብላት ደስ ይለኛል::
ማንበብ እጅግ በጣም ደስ ይለኛል! ያዝናናኛልም ጭምር! ለvacation ቢሆን ከሰብሊ ጋር ዉሀ ዳርም ከሆነ ቁጭ ብዬ ሳነብ ደስ ይለኛል ፊልም ማየትም በጣም ያዝናናኛል ከባለቤቴ ጋር አልፎ አልፎ እናያለን።
ከልጆቼ ጋር ከሰብሊ ጋር እንደህፃን ስጫወት ደስ ይለኛል። የሚያስከፋኝ ነገር ስንፍና ነው።
እንደውም እፈራለሁ ጓደኛዬም ማድረግ አልችልም ውስጤም ይሸሻል ግን የሚያስከፋኝ የምለው ነገር የለም ብዙ ፖስቲቭ ልምምድ ስላደረኩ ብዙ ነገር የለም።

ቀንዲል: አርአያዬ ነው የምትለው ወይም ተፅኖ የፈጠሩብህን ሰዎች እስቲ ንገረን?

ነፃነት : ኦ ብዙ ሰዎች በተለያየ ዘርፍ አርአያዬ ናቸው ከእናቴ ከአባቴ ብዙ ተምሬያለሁ ከዴል ካርኔጊ መጀመሪያ የሱን መፅሀፍ ነው ያነበብኩት ቀናነት ላይ፡ብዙ ተመሬያለሁ ሮበርት ካዮሳኪ ፋይናንሻል ህይወቴን ላይ ብዙ ተፅኖ ነብረው በሊደርሺፕ እና ቲም ወርክ ከጆን ሲ ማክስዌል እከተላለሁ::
ስለአይምሮ የጆሴፍ መርፊን መፅሀፍ በጣም እከተለዋለሁ::
ሮንዳን The secret በየቀኑ ደጋግሜ አየዋለሁ
ብዙ ናቸው ተፅኖ የፈጠረብኝ ባለቤቴ ሰብሊ ዛሬ ላለሁበት ከፍታ እሷ ሳታውቀው በማንነቷ ውስጥ ስትኖር እኔ በብዙ መልኩ ቀርፃኝ ዛሬ ላይ እየኖርኩ ያለሁበት ከፍታ አለ። በቡድናችን በቅን ቡድን ውስጥ ድንቅ መሪዎች አሉ:: የሚገርም ማንነት አያለሁ በተቻለኝ መጠን በዛ ማንነት እኔን እንዲቀርፀኝ አደርጋለሁ ለነሱ ባልነግራቸውም ሜንተሬ ናቸው::
ስኬት ላይ ሀይሌ ገብረስላሴ ከስኬቱ በስተጀርባ ያለው ማንነቱ:ይገርመኛል!
ቴዲ አፍሮ ትልቅ ከፍታና ቫይብሬሽን ያለው ሰው ነው ከሱም እማራለሁ ብቻ በተለያየ መልኩ ብዙ አሉ!

ቀንዲል : መፅሀፍ ታነባለህ ወይ?
ካነበብካቸው መጽሀፍቶች ውስጥ የሰዎች ህይወት እድገት ላይ ተፅኖ ይፈጥራል የምትለውን አንዱን እስቲ ለአንባቢያን ጠቁምልን?

ነፃነት :መፅሀፍ አነባለሁ::
ላለፉት አስር አመታት አካባቢ በየጊዜው የማነበው እንደሪፈረንስ የምጠቀመው "The power of your subconsious mind" የሚለው ነው እሱን ቢያነቡት አበረታታለሁ::

ቀንዲል: በቀጣይ ከነፃነት ምን እንጠብቅ?

ነፃነት : በቀጣይ ከነፃነት ምን እንጠብቅ? ለሚለው የኢትዮጲያ ህዝብ እንዳለ ማይንድ ውስጥ ፕሮግራም የሚሆንበት የአስተዳደር ሲስተም ኢትዮጲያኒዝም ብዬዋለሁ::

እሱን እየፃፍኩ ነው እያለቀ ነው ኢትዮጲያዊያንን ቅድም በጠቀስኩት ኢትዮጲያዊነት መምፈስ ውስጥ እንዲኖሩ ስልጣን አቅም ስለሆነ ስልጣን ላይ ያሉ የሚሰሩት ካልሆነ አንድ ቀን ስልጣን ላይ የሚወጣ የሚተገብረው ምናልባት አስተዳደር ላይ ያሉትም ጨምሮ ተፅዕኖ ፈጥሮ እንዲተገብሩት ሀገራችንን እንደምንናፍቃት እንደምንፈልገው እንደምንዋደደው እንድምኖር የሚያደርግ መፅሀፍ ይኖራል።
ከማናውቀው የውሸት ከሆነው ከተቀባባነው ማንነት ወጥተን ወደ ጀግንነት ወደ ፍቅር ወደ መደናነቅ ወደ ህብረት የሚያመጣንን እሱን ወደ ኢትዮጲያ ማቅረብ እንዲፈፀም የድርሻዬን መወጣት ነው።
- ሌላው የቴሌቭዢን ፕሮግራም ነው የpersonal development ለረጅም ጊዜ ቀርጬዋለሁ ትክክለኛውን ጊዜ እየጠበኩ ነው። ሰው ቤቱ ተቀምጦ የሚያየው ይኖራል::
ሌላው መዲናችንን በአበባ ቅርፅ የሚሰራ ላንድ ማርክ ለኢትዮጲያ ይገነባል አዲስ አበባ ታወር የሚባል!
የpersoanl development ሲዲዎች ሁለት አሳትሜያለሁ "እንዴት ልመን እና ቀና አስተሳሰብ እንዴት ልገንባ?" የሚል ስለዚህ በዋነኛነት ይሄንን ይመስላል።

ቀንዲል : ለወጣቶች ማስተላለፍ የምትፈልገውን መልዕክት ካለ?

ነፃነት : ለወጣቶች ማስተላለፍ የምፈልገው መልዕክት እናንብብ! ፖለቲካ ሳይሆን ህይወታችንን እናንብብ መለወጥ ያለብንን ማሳካት የምንፈልገውን መድረስ የምንፈልግበት ቦታ ሁሉ መድረስ ይቻላል። እዛ ለመድረስ ግን ህሊናችን መስራት አለበት ህሊናችን እንዲሰራ ትክክለኛ አይምሮአችንን የሚያሰራ መፅሀፍ ማንበብ አለብን የግል ልህቀት ላይ የሚሰራ መፅሀፍ እናንብብ ያነበብነውን በተግባር መተግበር ከዛም ራስ ላይ መስራት እጅግ በጣም ወሳኝ ነው ይሄንን እንዲያደርጉ እመክራለሁ!

ቀንዲል: እኔ ጥያቄዎቼን ጨርሻለሁ አንተ ቀረ የምትለው ነገር ካለ?

ነፃነት :በመጨረሻ አንደኛ እዚ ፕሮግራም ላይ ስለጋበዝሽኝ አመሰግናለሁ::
ሁለተኛ በጎ ስለሚያስቡ ሰዎች ሁሉ በየቦታው በግላቸው በጎ ሚያስቡ በጎ ሚጥሩ ሰዎችን ላመሰግን እወዳለሁ!
አንድ በጎ ሰው ካለ ለብዙ ይተርፋል ሰለዚህ በዛው እንዲፀኑ ተስፋ እንሲያደርጉ አምነው እንዲቀበሉ ከልቤ እፈልጋለሁ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ::

ቀንዲል : እኛም በአንባቢያን ስም እጅግ በጣም እናመሰግናለን። የዛሬው የአውደ ብሩሀን ገፅ እንግዳዬ በመሆን ከብሩህ ገፆችህ ስላቋደስከን ደስ ብሎናል። እናመሰግናለን።

በ ሳኦል አክሊሉ
aklilu7kemal@gmail.com

ጥቁር ምስል

እንደምንም እየከበደውም ቢሆን አይኑን ገለጠው። ከእንቅልፉ በትክክል አልነቃም። አንድ አይኑን ብቻ በከፊል በመግለጥ አጠገቡ ያለውን ሰዐት ተመለከተው ፤ ከቀኑ 8:30 ሆኗል። ሰዐቱን ሲያይ እንደሌላው ጊዜ አልደነገጠም፤ ቀኑና ምሽቱ ተገለባበጥውበት ከሰው በተቃራኒ መኖር ከጀመረ እንደቀልድ አንድ አመት ሊሞላው ነው። ዉሃ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው እንዲሉ እሱም እየሳቀ የጀመረውን የህይወቱ ጥቁር ገፅ እያለቀሰ መግለጥ አቅቶታል። አንገቱን ወደ ግራ ለማዞር ሲል አንገቱ ላይ ተሰምቶት የማያውቀው የህምም ስሜት ተሰማው ፤ ከሰአታት በፊት ጆሮ ግንዱ ላይ ያረፈበት ቡጢ ትዝ አለው። እንደ ምንም ታግሎ ወደ ግራ ተንከባለለ ፤ ሊያያት የፈለጋት ሴት ግን አጠገቡ የለችም። ትራሷ ላይ የተቀመጠው ወረቀት መርዶ እንደያዘ ገብቶታል፤ ግን እንደምንም ደፍሮ አንስቶ አነበበው ‘ላልመለስ ሄጃለሁ፤ ለምን ሄደች ከማለትህ በፊት ራስህን በመስታውት እየው’ ይላል ወረቀቱ። ተነስቶ እ

የተጣደፈ መስታውቱ ፊትለፊት ቆመ።

ለሰዐታት ከመስታውቱ ጋር ተፋጠጡ ፤ የሚያየው ነገር ምንም አልገባህ አለው ፤ መስታውት ፊት ቆሞ የማያውቅ እንግዳ መሰለ፤ አይኑን እና ጉንጮቹን እየነካካ ወደ መስታውቱ ለማየት ሞከረ፤ መስታውቱ የሚያሳየው ምስል ግን ሌላ ነው። ፈራ፤ በግንባሩ ላብ ግጥም ሲል ታወቀው፤ ‘ደከም ባለ ድምፅ ለምንድን ነው መስታውቱ ጥቁር የሆነው’ አለ ለራሱ። የፍርሃት መጠኑ ሲጨምር ግራ እንደተጋባ ስልኩን አንስቶ ደወለ።

‘ሶኒ ቶሎ ና ፤ አስቸኳይ ነው እባክህ’ ስልኩን ዘግቶ መስታውቱ ላይ አፈጠጠ። ብዙም ሳይቆይ የተደወለለት ጓደኛው ሶኒ በሩን ከፍቶ ገባ ፤ ሮጥ ብሎ ወደ መኝታ ቤት ሲገባ ቃለአብ ከመስታውቱ ጋር እንደተፋጠጠ ነበር። ሶኒ ወደ ቃለአብ እያየ ‘ስማ እስካሁን አልተዘጋጀህም እንዴ፣ 11:30 ሆኗልኮ’ ። ቃለአብ ድጋሚ የድንጋጤ ሀይቅ ውስጥ ገባ ‘መስታውቱ ፊት ከቆምኩ ሶስት ሰአት ሞላኝ ግን የማየው ነገር ምንም አልገባኝም?!’ አለ ህልውናውን እየተጠራጠረ።

ሶኒ በግርምት አንዴ ቃለአብን አንዴ መስታውቱን ተገርሞ ካየ በኋላ ‘ደሞ ብለህ ብለህ መስታውት ገልብጠህ ማየት ጀመርክ’ ብሎ መስታውቱን ገለበጠው። መስታዉቱ ሲገለበጥ በመስታዉቱ የሚያየው ሰው ምስል አስፈራው፤ እንደመጀመሪያው አይኑን እና ጉንጮቹን እየነካካ ወደ መስታውቱ ለማየት ሞከረ ፤አሁን በመስታውቱ ውሰጥ የሚያየው ሰው ጉንጬ በልዟል፣ የከንፈሩ ጥቁረት ጨለማን ያስንቃል፣ ራሱን እያየ አልመስል አለው ፤ ድንገት ሳያስበው ‘ፊትለፊት ያለው ሰውየ ግን ለምን ዘወር አይልልኝም?!’ ብሎ በብስጭት ጮኸ። ወዲያውኑ በንዴት መስታውቱን ገለበጠው ፤ ‘ያንን ቀፋፊ ሰው ከማየት ይህንን ጥቁር ምስል ብመለከት ይሻለኛል’ አለ አሁንም በብስጭት። ድጋሜ ጥቁሩን ምስል እያየ ደቂቃዎች ነጎዱ ፤ ሶኒ በትግስት ሲያየው ከቆየ በኋላ ከተቀመጠበት ተነስቶ ‘ይህንን የሀሺሽ ሱስ የማታቆም ከሆነ እንኳን ሮዛ ቃለአብም ጥሎህ መሄዱ አይቀርም’ አለ ድምፁን በብስጭት ከፍ አድርጎ። ‘የጀመርኩት መንግድ መሄጃ እንጅ መመለሻ የለውም’ አለ ቃለአብ ጥቁሩ ምስል ላይ እንዳፈጠጠ። ሶኒ ከቅድሙ በላይ ተበሳጭቶ ‘እንግዲያውስ ከዚህ አስፈሪ ሰው ጋር ህይወትህን ቀጥል’ ብሎ መስታውቱን ገልብጦት እየተንደረደረ ሊወጣ ሲል ‘እባክህ ቆይ’ አለ ቃለአብ ድክም ባለ ድምፅ። ሶኒ ቆመ ፣ ወደኋላ ዞሮ ቃለአብን ሲያየው አዘነለት፤ አንድ ቃል እስኪተነፍስ ድረስ አይን አይኑን ሲያየው ከቆየ በኋላ ቃለአብ መናገር ጀመረ ‘አንዴ ጠብቀኝ’ ብሎ ወደ መታጠቢያ ቤት ሄደ። ሶኒ እንደቆመ የቃለአብን ክፍል ለማየት ሞከረ ፤ መኝታ ቤቱን ማፅዳት አይደለም ማየት በራሱ ያደክማል፤ አእምሮው በሃሳብ ተወጥራ ልትፈነዳ ስትደርስ በረጅሙ ተነፈሰ፤ በትንሹም ቢሆን ሰላም ተሰማው፤ ራሱን ማረጋጋት ሲጀምር ያልጠበቀው ድምፅ ጆሮው ውስጥ ገባ ፤ ወዲያው ድምፁን ወደሰማበት መታጠቢያ ቤት ሮጠ …

………………..ይቀጥላል…………………..

በናሆም ሸዋንግዛው
ShewanGizawna-
hom@gmail.com

ምስለ ሙሰለኒያን

ብዝሃነትን የተላበሰችዋ ወደ አራት ግድም የሚጠጉ ብሄራዊ የስራ ቋንቋዎች በስራ ላይ ያሉባት ፌደራሊዝም ሲነሳ ብዙዎች እንደምሳሌ የሚጠቅሷት የባህር በር አልባዋ ስዊዘርላንድ ነች። በሀያኛው ምዕተ ዓመት መባቻ ላይ በርከት ያሉ የጣልያን ስደተኞች በስዊስ አገር በተለያዩ ሙያዎች ላይ ተሰማርተው ሰላማዊውን የዕለት ተዕለት ኑሯቸውን ይገፉ ነበር። በሌላኛዋ የአውሮፓ መዲና በሆነችው ጣሊያን በሮምኛ አውራጃ ስራኖ ዴይ- ኮስታ በተባለች ወረዳ ተወልዶ ያደገው በአመጸኛነቱና በአስቸጋሪነቱ ማህበረሰቡን ያስቸገረው ቤንቶ- አምቢከር - አንድሬአ - ሙሶሊኒ አዲስ ህይወት በመሻት ከትውልድ ቄው ተሰደደ። በ1902 እ.ኤ.አ የጣልያን ስደተኞችን ተቀላቀላቸው። ከዛም በተለያዩ የጉልበት ስራዎች ላይ አጋዥ በመሆን እየለፋ በሚሰራበት ጊዜ የተንኮል መርዙን አውጠንጥኖ ለመርጨት ያደባ ጀመር።

የያዛትን ስልጣን ተንተርሶ ስደተኞቹን ሰብስቦ አሠሪዎቹ በሠራተኛ ላይ የሚያደርሱትን ግፍና የስዊዝ መንግስት ለጥቅሙ ሲል ባለገንዘቦችን ምን ያህል እንደሚረዳ ሲነግራቸው፣ ሲያብራራላቸው ሁሉም በደስታ ተቀበሉት። የሰላማዊ ሰልፍም ቀን ቆረጠላቸው፤ እሱ በቆረጠላቸው ቀን "ተበደልን፤ግፍ ትፈፀመብን!!" እያሉ በመጮህ ተሰልፈው በከተማ ሲርመሰመሱ፥ ጄኔቭ አይታ በማታውቀው እንግዳ ክስተት ደነገጠች። የሰልፉን ተቀዳሚዎች ቢሮ አግብተው "መብታችሁ ምን ላይ እንደተጓደለ? ጭቆና እንደደረሰባችሁ ብትነግሩን ለማድመጥ ዝግጁ ነን::" አሏቸው፤ በስማበለው የተማገሩት ሰልፈኞችም መልስ ጠፋቸው። ሙሶሊኒም በስዊስ የመኖርያ ፍቃድ አልነበረውም፤ ያሰበውን ሸፍጥ ለማስረዳት ሳይቻለው ቀረ፤ ሰልፈኞቹም እንደተሸወዱ ገብቷቸው ይቅርታ ጠይቀው ወጡ። ይህን ከላይ ያለውን ሀሳብ የከተብኩት በጥልቀት ከተብራራበት "የቀዳማዊ ኃይለስላሴ መንግስት" ከሚለው የአምባሳደር ዘውዴ ረታ መፅሀፍ ላይ ነው። እኔም ይህን ማንሳቴ... ታዲያ እጅ ከምን?... ካስባለኝ.. ድሮና ዘንድሮ አንድ ሲሆኑብኝ ፤ የታሪክ ትልሙ ውሉን ሲስትብኝ... ብዕሬን አነሳሁ...። "ኤዞፕ" ታሪክ አንብቦ "ምን ተረዳህ" ቢሉት "ሰው ከታሪክ እንደማይማር"... ያለው በኛ ደረሰ ፤ለዛውም በኛ ዘመን!! ታሪክ ባለፈው ዘመን የተከሰተ የሰዎች የጋራ መስተጋብራዊ ውጤት ሲሆን ፤ ትልሙም ካለፈው በመማር፣ ዛሬያችንን ለመረዳት ብሎም ነጋችንን ለመተለምና ለመተንበይ ከማገልገል አልፎና ተርፎ (ከመማሪያነት በዘለለ መልኩ) ዛሬ ላይ እዳ የሚከፈልበት ፈሊጡ አይገባኝም.... ጋሽ አሌክስ

"የአባት እዳ ለልጅ ይባል ነበር ድሮ :
ባ'ያት እዳ ገባሁ እኔማ ዘንድሮ ..."

ወጣቱ ታሪኩን እየተረዳ ስለራሱ ሌሎች ለአላማቸው ቆንፅለው የሚሰጡትን የተንሻፈፈ ታሪክ ለመሞገት ይረዳው ዘንዳ ታሪኩን አንብቦ ተረድቶ ከታሪክ ተምሮ ነገውን የተሻለ እንደማድረግ በእነ ምስለ-ሙሶሊኒ ሴራ ተጠልፎ የኢ-ሃሳባዊያን እኩይ አላማ ማስፈፀሚያነት እራሳቸውን ይጥብቁ ዘንዳ ግድ ይላቸዋል። በታሪክ ምስለ ሙሶሊኒያውያን ተመላልሰው ይመጣሉ። በአሁኑ ጊዜም በዘር፣ በደም እየከፋፈሉ ወጣቱን እያዘናጉ፤ ወጣቱም መጠየቁን ትቶ በጭፍን መከተሉን ሲያውቁ እንደዱላ ለመጠቀም ተመቻቸው - መርዛቸውን መርጨት ጀመሩ፤ ወጣቱን እያደነዘዙ እሱም ማደንዘዣውን ለመቀበል ክፍትና ቀላል ስለሆነ። ስሜቱን እያጋሉ ከታሪክ ውስጥ ያልነበረውን በአፈታሪክ ጀቡነው እውነት አስመስለው ስሜቱን እየናጡት "እኔ አውቅልሀለው ፣ እኔ አስብልሃለው።" እያሉ በቆረጡለት ቀን ሰልፍ እየማገሩት: ይህን ምስኪን ነገውን እያጨለሙበት ነው ።

"እኔ አውቅልሃለው" ከሚለው እኩል፣ ከሚነዳው እኩል ነገሩን የተረዱ አርቆ አሳቢና አስተዋይ ወጣቶች እኩል የነሱ ዝምታም ለጥፋቱ የራሳቸውን ድርሻ ይወስዳሉ። ምክንያቱም የአዋቂው ዝምታ ከመሀይሙ ጫጫታ እኩል አጥፊ ነውና።

ከሰልፉ በኋላ ሙሶሎኒም ከማህበር ሃላፊነቱ ሲሸሩት፣ ስዊስ ከሀገሯ አባረረችው። እኛም ምስለ-ሙሶሊኒዎችን ማክሰም ምንችለው በማባረርና በማውገዝ ሳይሆን፣ በቡድን ማሰብን እምቢ አሻፈረኝ በማለትና ሌላው በችግር ጊዜ አንድ በሚያደርገን ስውር ስፈትታዊ ልዩ ኃይል ለጥካሬ አንድ በመሆን ለማሰብ እንደግል በመሆን የጋራ ጠላት የሆኑትን ምስለ-ሙሶሎኒያንን እየመከትን "እ... ና... ከ... ሽ... ፋ... ቸ... ዋ... ለ... ን" እንጂ "እ...ን... ከ... ሽ...ፍ... ም"።

ሰላምና ፍቅር ብሎም አንድነት ለኢትዮጵያችን
ቸር እንሰንብት

ቀንዲል
MOBILE APP
LIVE KENDIL STREAMING
LATEST UPDATES
ቀንዲል DIGITAL MAGAZINE
KENDIL
Digital Magazine
MOBILE
APPLICATION
SEARCH OUR TELEGRAM CHANNEL .K.
ENDILM AND INSTALL THE APPLICATION
FOR OUR LATEST MAGAZINE UPDATES

የትውልዳችን አዕምሮ ልሂቃን

በአለማችን በርካታ አስገራሚ አዕምሮ ያላቸው ሰዎች ይገኛሉ:: የአዕምሮ ብቃታቸው (አይ ኪው) 140 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ልዩ ብቃት እና እውቀት የተላበሱ መሆናቸው ይነገራል። ከአለማችን ህዝብ 0.5 በመቶ የሚሆኑት የምጡቅ አዕምሮ ባለቤት መሆናቸውንም ነው መረጃዎች የሚያሳዩት።
ከዚህ በታችም በምድራችን በ2018/2019 አጃኢብ የተባለላቸውን 10 ድንቅ አዕምሮ የተቸሩ ሰዎችን እና የአስተሳሰብ ልህቀታቸውን ወይንም አይኪው(IQ) እንመለከታለን። ከሁሉ በፊት ግን ትንሽ ስለ አይኪው(IQ) እናውራ :: አይኪው(IQ) ማለት የአይምሯችንን የአስተሳሰብ ፍጥነት የሚለካበት ቁጥር ነው :: ይህንንም ምናገኘው በተወሰኑ የአይምሯችንን የአስተሳሰብ ፍጥነትን ይለካሉ ተብለው የተዘጋጁ ጥያቄዎችን በመመለስ ያገኘነውን በመቶ ተባዝቶ የሚመጣ ነው :: አማካዩ ወይም መደበኛው የIQ ቁጥር መቶ ሲሆን ከዛ በላይ የሚያመጡ ሰዎች ድንቅ የአይምሮ ብቃት ባለቤት መሆናቸው ይነግራል::

እነሆ! የዘመናችን ድንቅ አይምሮ ባለቤቶች

ስቴፈን ሀውኪንግስ

በወጣትነት ዕድሜያቸው በደረሰባቸው አደጋ በህይወት የሚቆዩት ለሁለት ዓመታት ብቻ እንደሆነ ቢነገራቸውም ታላላቅ ሳይንሳዊ ግኝቶችን ለዓለም እያበረከቱ ተጨማሪ 50 ዓመታትን በዚህች መድር ላይ የኖሩት ሀውኪንግ አይ ኪዋቸው 160 መሆኑ ይነገራል።
በፊዚክስ እና በህዋ ሳይንስ በርካታ ስራዎችን ለአለም ሰርተዋል።
ሰባት በብዛት የተሸጡ መፅሀፍትን ከማሳተማቸው ባለፈ 14 ትላልቅ ሽልማቶችንም ተረክበዋል። ሀውኪንግ ባሳለፍነው የፈረጆቹ አመት ከዚህ አለም በሞት ተለይትዋል::

ኪም ኢንግ ዮንግ

ይህን ኮርያዊ ፕሮፌሰር የአለም ድንቃ ድንቅ መዝገብ ከፍተኛ የአዕምሮ ብቃት ካላቸው ሰዎች መካከል እንዲካተት አድርጎታል።
በሁለት አመቱ አራት ቋንቋዎችን መናገር የቻለው ዮንግ በስምንት አመቱ ነበር በአሜሪካ እንዲማር ናሳ የጋበዘው። በስምንት አመቱም ነበር phd ከኮሎራዶ ዩንቨርስቲ የተቀበለው :: ኪም ኡንግ በአራት አመት እድሜው ነበር ከፊዚክስ ቀመሮች ጋር የተተዋወቀው :: የአዕምሮ ብቃቱ (አይ ኪው) 210 መሆኑም ተጠቅሷል። የ 52 አመቱ ኪም በትውልድ ሀገሩ ሺሻም በሚባል ዩንቨርስቲ በማስተማር ስራ ላይ ይገኛል::

ፖል አለን

ከአለማችን ቁጥር አንዱ ባለጠጋ ከቢልጌት ጋር በመሆን 1975 የአለማችን ግዙፉን የኮምፒውተር ሶፍትዌር ካምፓኒ ማይክሮ ሶፍትን የመሰረተው ፖል አዕምሮውን ወደ ገንዘብ የቀየረ ስኬታማ ሰው መሆኑን በርካቶች ይመሰክሩለታል። ፓል በ2007 እና 2008 የታይም መፅሄት 100 የአለማችን ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ዝርዝር ውስጥ ለመካተት በቅቶም ነበር:: ከማይክሮሶፍት በተጨማሪ በርካታ ድርጅቶችን አፍርቶም ነበር :: ከነዚህም ውስጥ የስነ-አይምሮ ሳይንስ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የህዋሳት ሳይንስ ማዕከላት ይገኙበታል :: ፓል በህይውት በነበረበት እና በስኬት በኖረባቸው አመታት በየአመቱ 2 ቢልዮን ዶላር ለበጎ አድራጎት ያውል ነበር :: ፓል አልን ባሳለፍነው የፈረንጆቹ አመት 2018 ከዚህ አለም በሞት መለየቱ ይታወሳል:: ፖል 21 ነጥብ 2 ቢሊየን የአሜሪካ ዶላር ሀብት በማስመዝገብ የአለማችን 44ኛው ባለጠጋ ነበር ::

ሪክ ሮንሰር

በ1960 በሀገረ አሜሪካ የተወለደው ሪክ እንደነ ፖል አለን በሀብት ማማ ላይ መቀመጥ ባይችልም አይ ኪዉ 192 ነው። ሮንሰር በቅርቡ ጂሚ ኪመል በሚያዘጋጀው ተወዳጅ የቴሌቪዥን ሾው ላይ በስክሪፕት ፀሃፊነት አገልግለዋል፡፡በቴሌቭዥን ፀሐፊነቱ ከመታወቁ በፊት በብዙ ቡና ቤቶች ውስጥ በአስተናጋጅነት መስራቱን ይናገራል:: ሪክ የ58 አመት ጎልማሳ ነው::

ጌሪ ካስፕሮብ

ሀገረ ሩስያዊው ካስፕሮቭ 1963 ባኩ በምትባል ከተማ ተወልዶ አድጎዋል:: በ22 አመቱ የአለም የቼዝ ሻምፒዮን መሆን የቻለው ካስፕሮቭ፥ በ2005 ራሱን ከስፖርቱ አለም አግልሏል። በአሁኑ ወቅት በፖለቲካው መስክ በመሳተፍ እና በመፃፍ ጊዜውን እያሳለፈም ይገኛል። አይ ኪዉ 190 የሆነው ካስፕሮቭ በሩሲያ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ መወዳደሩ ይታወሳል።

ሰር አንድሪው ዊልስ

በ1995 በአለማችን ከባድ የሚባለውን ውስብስብ የሂሳብ ስሌት የፈቱ ሲሆን፥ በሂሳብ እና ሳይንስ ዘርፎች 15 ሽልማቶች ተበርክቶላቸዋል። አንድሪው ፌርማት የሚባለውን የሂሳብ ቲዎሪ ወይም ፅንሰ ሀሳብ በመፍታት በስፋት ይታወቃሉ:: የእኝህ የሂሳብ ሊቅ የአዕምሮ ብቃት ልክ 170 መሆኑም ተመልክቷል። ከኦክስፎርድ ዩንቨርስቲ በፕሮፌሰርነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ::

ክሪስቶፈር ሂራታ

አሜሪካዊው ሂራታ “international physics olompiad” የወርቅ ሜዳልያ ሲያሸንፍ ገና የ13 አመት ታዳጊ ነበር:: በ16 አመቱ ናሳን የተቀላቀለው ሂራታ በ22 አመቱ በአስትሮፊዚክስ የዶክትሬት ዲግሪውን አግኝቷል። " colonization of mars" በተሰኘው ሰፋ ያለ ሪሰርቹም ይታወቃል:: በአሁን ሰአትም ሂራታ በኦኤስዩ ሴንተር በኮስሞሎጂ እንዲሁም በአስትሮ ፓርቲክል ፊዚክስ በፕሮፌሰርነት በማገልገል ላይ ይገኛል:: የምጡቅ አዕምሮ ባለቤት ናቸው የሚባሉት ጭምር ይቀኑበታል የተባለው ሂራታ አይኪዉ 225 ነው።

ጁዲት ፖልጋር

ሀንጋራዊት ስትሆን ውልደትዋ 1976 ነው:: ህፃናት ከለጋ እድሜያቸው ጀምሮ በልዩ ልዩ የትምህርት አይነቶች መሰልጠን አለባቸው ብለው በሚያምኑ አባቷ ያደገችው የ35 አመቷ ፖልጋር፥ በ15 አመቷ ቦቢ ፊሸር የተሰኘውን ታዋቂ የቼዝ ተጫዋች በመርታት ስሟን በጉልህ አፅፋለች። ፓልጋር በጊዜው የአለምን ቁጥር አንድ ቼዝ ተጨዋች የነበረን ተጨዋች በማሸነፍ እና ወደ አስራንድ ጊዜ የሚጠጉ የአልም የቼዝ ሻምፒዮኖችን በማሸነፍ ብቸኛዋ ሴት ተጨዋች ነች :: የፖልጋር አይኪው 170 ነው።

ትሬንስ ታኦ

በ2 አመቱ መሰረታዊ አርቲሜቲክ መስራት ችሏል፤ በ20 አመቱ ደግሞ ከፕሪንስተን የዶክትሬት ዲግሪውን ተቀብሏል። በ13 አመቱ በአለም አቀፍ የሂሳብ ውድድር ያሸነፈው ታኦ ከ230 በላይ የምርምር ውጤቶችን አሳትሟል። እስካሁንም ከ21 ያላነሱ ሽልማቶችን የተበረከተለት የምጡቅ አይምሮ ባለቤት ነው :: ይህ የአሜሪካና የአውስትራሊያ ዜግነት ያለው ባለፍጣን አዕምሮ የ36 አመቱ ጎልማሳ አይኪው 230 መሆኑ ተጠቅሷል። ታኦ የፊልድስ አዋርድ ተሸላሚ ሲሆን የመጀመርያው አውስትራሊያዊ ያደርገዋል::

ጀምስ ውድስ

በ ሊኒየር አልጀብራ (linear algebra) እጅግ የተካነ መሆኑ የሚነገርለት ውድስ በአሁኑ ወቅት ከትምህርት አለም የራቀ ቢሆንም ሶስት የኤሚ አዋርዶችን ተቀብሏል:: የውድስ አይኪው 180 ነው።

ለዛሬ በዚህ አበቃሁ በቀጣይ ዕትም በወቅታዊ እና እጅን በአፍ በሚያስጭኑ ድንቅ እና አነጋጋሪ ጉዳዩችን ይዤ እቀርባለሁ። እስከዛው ቸር ያቆየን!

——ሰላም‼——

በ ፍራኦል መስፍን
(በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ሌክቸረር እና ሀኪም)
(fraolmesfn8@gmail.com)

እራስን ማወቅ

Self Awareness

አንድ ሰው ውጤታማ ለመሆን በበቂ ሁኔታ ራሱን ማወቅ/ መረዳት አለበት። ሰው ስለ ራሱ ማወቅ ከሚገባው በርካታ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ስለራሱ ስሜትና ማንነት ነው። ስሜትን ወይም ማንነትን ለመረዳት የራስን ባህሪ፤ ፍላጎትና ችሎታ ማወቅ እንዲሁም በህይወት ውስጥ እና በማህበረሰብ ውስጥ ስለሚሰጠው ቦታ መረዳትን ይጠይቃል።
ማንነት ሁለት አይነት መገለጫዎች አለው። ውስጣዊ መገለጫ እና ውጫዊ መገለጫ ። ውስጣዊ መገለጫ ከውስጣችን ወደ ውጪ የሚገለጥ ሆኖ ያለን አቅም፤ ፍላጎት፤ ችሎታና ስሜቶች ያካትታል። ውጫዊ ስንል ደግሞ ሌሎች ለኛ የሚሰጡን መገለጫዎች ናቸው። ይህም ተክለ ሰውነት፤ ስያሜ፤ ሀይማኖት፤ የትውሌድ ቦታ፤ ባህል፤ ጎሳ ወይም ዜግነት የመሳሰሉትን ያካትታል።

ከላይ የተዘረዘሩት የማንነትና የስሜት መገለጫዎች በመለየትና በመረዳት ስለራሳችን ያለንን ግንዛቤ ማሳደግ እንችላለን። ይህም ግንዛቤ/ ስለ ራስ ያለ እውቀት ሁኔታችንን በተመለከተ በቂ መረጃዎች በመሰብሰብ ትክክለኛ የራስ ግምገማ ለማካሄድና የራሳችንን ጠንካራና ደካማጎን ለመለየት ያስችለናል። አንድ ሰው ስለ ራሱ ባለው እውቀት መነሻነት የሚያደርገው የራስ ግምገማ በራስ የመተማመን ክህሎቱን ለማጎልበት ይረዳዋል። የሚሰማንን ስሜትና ማንነትን ማወቅ እራስን ለመቆጣጠር ያስችላቸዋል።
ራስን መግለጽ ማለት የምንፈልገው ምን እንደሆነና ለምን እንደምንፈልገው የመግለጽን እንዲሁም ያመነውን ለማሳካት ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን መውሰድን ያጠቃልላል።
ራስን መግለጽ በተለያዩ ሁኔታዎች ሊንጸባረቅ ወይንም ሊገለጽ ይችላል። ለምሳላ በትምህርት ቤት ከጓደኛዋ ወይንም ከሌላ ሰው የሚቀርብላትን የወሲብ ጥያቄና መገፋፋት እንቢ አይሆንም የምትል ተማሪ፣ ትምህርት መቀጠል መፈለጋቸውን ወላጆቻቸው እንዲያምኑበት የሚያደርጉ ህጻናት ፣ የአካባቢያቸውን የማህበረሰብ አባላት በማሳመን በአንድ ላይ ለአካባቢያቸው ጠቃሚ የሆኑ የተፈጥሮ ሃብቶችን ለመጠቀም የሚንቀሳቀሱ ወጣቶች ተግባር ወ.ዘ.ተ ራስን ከመግለጽ ጋር ይያያዛሉ።

ራስን የመግለጽ ችሎታ ከባህል ጋር ተዛማችነት ያላቸው ሁኔታዎች ይንጸባረቁበታል። ህጻናትም ሆነ በጉርምስና ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወጣቶች እንዴት በሁሉም ሁኔታዎች ራሳቸውን ለመግለጽ እንዳለባቸው ወይንም እንደሚችሉ ማወቅ አለባቸው። ከእነዚህም በተጨማሪ ህጻናትና ወጣቶች ከጓደኞቻቸው ጋር ሲሆኑ ራሳቸውን የሚገልጹበት መንገድና ከወላጆቻቸውና ከመምህራኖቻቸው ጋር ሲሆኑ ራሳቸውን የሚገልጹበት መንገድ ይለያያል።

የራስን ስሜትና ማንነት መረዳት
ጥልቅ ስሜት፡- ማለት ከውስጣችን ወይም ከአካባቢያችን ጋር በሚኖረን መስተጋብር የምንሰጠው ምላሽ ነው። አካላዊ ስሜትና አእምሮአዊ ስሜት ብለን ለሁለት ልንከፍለው እንችላለን።
አካላዊ ስሜት በሰውነታችን ክፍሎች በሚፈጠር ሂደት የሚሰማን ሲሆን ተፈጥሯዊ ነው። ለምሳሌ፡- ህመም፣ ረሀብ፣ ጥም፣ ሙቀት ። አዕምሯዊ ስሜት በስሜት ህዋሳቶቻችን ለ አዕምሮ መልዕክት ደርሶ በሚፈጥረው ምላሽ ይገለፃል ። ለምሳሌ ፡ ፍቅር፣ ንዴት ፣ ሳቅ ፣ ለቅሶ ።
ከራሳችን ሆነ ከሌሎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ውስጥ የሚሰሙንን የተለያዩ ስሜቶች በትክክል መረዳት ይኖርብናል። በዕለት ተዕለት ህይወታችን ውስጥ የሚሰሙን ስሜቶች ሊያሳድሩብን የሚችሉትን ተፅዕኖ አስቀድሞ መመርመርና መረዳት እንዲሁም በስሜታችን ጫና ብቻ ውሳኔዎችን እንድንወስን ያግዘናል። የራስን ማንነት ለመፈተሽ መሠረታዊ የሆኑ ማንነትን ለመረዳት የሚረዱ ጥያቄዎች ራስን መጠየቅ አስፈላጊ ነው።
ትክክለኛ የራስ ግምገማ
በተለያዩ ጊዜያትና ሁኔታዎች ውስጥ የሚሰማንን ስሜት ማወቅ አስፈላጊ ቢሆንም በቂ ግን አይደለም።

ሌሎች ስለራሳችን ማወቅ ከሚገቡን ነገሮች ፦ ስለራሳችን ጥንካሬ፤ ድክመት፤ የሚያሳስቡን ጉዳዮች፤ ያለን መልካም አጋጣሚ ማወቅ ይገባናል። የራሳቸውን ደካማ ጎን የሚያውቁ ሰዎች ገንቢ አስተያየት የሚቀበሉና ከሌሎች ለመማር ዝግጁ የሆኑ ናቸው። በዚያው መጠን ሰዎች ጠንካራ ጎናቸውን ማወቅና መጠቀም ይኖርባቸዋል።

በራስ መተማመን (self confidence)

እራስን ማወቅና የራስን ትክክለኛ ግምገማ ማድረግ ለራስ ትክክለኛ ግምት ወደ መስጠት ያመራል። በራስ መተማመን ማለት አንድ ሰው ስለራሱ በሚኖረው በቂ እውቀትና ትክክለኛ የሆነ ግምገማ በማካሄድ ካለው ጥንካሬ በመነሳት ስለራሱ የሚያዳብረው ብቃት/ እምነት ነው። በአፍላነት እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ልጆች በራስ መተማመን እንዲያዳብሩ ስላላቸው ጥንካሬና ድክመቶች መረዳት እንዲችሉ እድል ልንፈጥርላቸው ይገባል። ይህም በቂ ጊዜ ወስደው ስለራሳቸው ማሰላሰል፤ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን መመዘኛ መሥፈርትን እንዲያወጡና በዚህም ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን እንዲለዩና በየጊዜው ይህን ልምምድ እንዲተገብሩ ልናግዛቸው ይገባል። ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖረው ውጤታማ ግንኙነት ባለው የራስ መተማመን ብቃት ላይ ይመሠረታል። አዋቂ ሰዎች፣ ለምሳላ፦ ወላጆች፣ የቤተሰብ አባላት፣ መምህራን እና ጓደኞች ከዛ ሰው ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት የሰውዬውን በራስ መተማማን ስሜት ለመገንባትም ሆነ ለማፍረስ ከፌተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በዚህም የተነሳ የአንድ ሰው የራስ መተማመንን ክህሎት ለማጎልበት ከሰዎች ጋር የሚኖር አዎንታዊ ግንኙነት በጣም አስፈላጊ ነው።

ለራስ ትክክለኛ ግምት መስጠት(self esteem)

ሰዎች ስለችሎታቸውና በማህበረሰብ ውስጥ ስላላቸው ቦታ ሲያዉቁ ለራሳቸው ያላቸው አክብሮት እንዲሁ እየጨመረ ይመጣል። ለራስ ትክክለኛ ግምት መስጠት አንድ ሰው በውስጡ ያለውን ጥሩ ነገር የማወቅ ውጤት ነው ይባላል። ለራስ ትክክለኛ ግምት መስጠት ማለት ሰዎች ስለተክለ ሰውነታቸው፣ ስለችሎታቸውንና ስለባህሪያቸው ያላቸው ስሜት፤ አስተሳሰብና ድርጊት ውጤት ሲሆን ይህም ለራሳቸው፤ ለሌሎችና ለአካባቢያቸው በሚገልፁበት መንገድ ይገለፃል። ይህም እያደገና እየጎለበተ የሚመጣው የሚያከናዊኑት ተግባራትም ሆነ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸውና ተግባሮቻቸው ውስጥ የሚያሳዩትን ብቃትና ውጤታማነት መሰረት በማድረግ ነው። ለራስ ትክክለኛ ግምት ያላቸው ሰዎች ለችግሮች ለምሳሌ ፦ ጥንቃቄ የጎደለው የወሲብ ህይወት፣ ጫናና ውጥረት፣ ሲጋራ ማጨስ፣ የአልኮል ሱሰኝነትና አደንዛዥ ዕጾችን መጠቀም እና ለመሳሰለት እጅ አይሰጡም ይልቅ በችግር ውስጥ አልፈው የለሙትን ያሳካሉ።

ቸር እንሰንብት ! !

ፍራኦል መስፍን በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ሌክቸረር ሲሆን ፤ በ ሞያው የአዕምሮ ሐኪም ነው ::
E-mail: firaolmesfin8@gmail.com

በኤርምያስ ደጀኔ
ermiyasdejene@gmail.com



ሰላም ውድ የቀንዲል ዲጂታል መፅሔት ተከታታዮች በዛሬው የስነ ፈለክ ፅሁፋችን አለማችን ካስተናገደቻቸው እና የህዋን ሳይንስ አንድ ደረጃ ከፍ ያደረጉ የሶስት ታላላቅ ተመራማሪዎች የምርምር ግኝቶቻቸውን ላስነብባችሁ ወደድኩ እንደሚከተለው አጠር አድርጌ አቀርበዋለሁ።

Copernican system (1543)

እ.ኤ.አ በ 1543 በፖላንዳዊው አስትሮነመር ኒኮላስ ኮፐርኒከስ ታትሞ የወጣው "Copernican system" ቀድሞ ስለኮስሞስ ሲታመንበት የነበረውን መላምት "አፈር ደቼ "አስጋጠው። በኮፐር ኒከስ ንድፈ ሀሳብ መሠረት ፀሐይ የሶላር ሲስተሙ ማዕከል ናት። ምድርን ጨምሮ ሁሉንም በዕርሷ ዙርያ ይሽከረከራሉ። ከእርሱ በፊት ይታመንበት የነበረውን ንድፈ ሀሳብ "Ptolemaic system" ተብሎ ይጠራል። በዚህ ምልከታ መሠረትም ምድር የሁሉም ነገር እምብርት ናት ይል ነበር። ሌሎች ፕላኔቶች በምድር ዙርያ ሲሽከረከር የራሳቸውን ትናንሽ ክበባት በመፍጠር ነው! ይልም ነበር።
ኒኮላስ ግን የራሱን ሲስተም በሚመለከተው ሁኔታ ነበር ያስረዳው።
-የግዙፍ አካላት እንቅስቃሴ ወጥ ነው።
-ቅርፁ ክብ ነው።
-የዩንቨርሳችን እንብርት ወደ ፀሐይ የተጠጋ ነው።
-በፀሀይ ዙርያ ፕላኔቶች ይዞራሉ።
ስለ ኮፐርኒከስ ይሄንን ካልን ከዚህ አስከትለን ደግሞ የህዋ ሳይንስን አንድ ደረጃ ከፍ ካደረጉ ሰዎች መካከል የዮሐንስ ኬፐለር ንድፈ ሀሳብ የሆነውን Kepler's law of planetary motion አጠር አድርጌ ላሳያችሁ ወደድኩ።

Kepler's laws of planetary motion(1609)

ጀርመናዊው የስነ ክዋክብት ተመራማሪ የሆነው ዮሐንስ ኬፐለር ስለ ፕላኔቶች እንቅስቃሴ የሚያስረዳ የመጀመሪያ ሁለት ህጎቹን በ1609 ሦስተኛውን ደግሞ ከ10 አመት በኋላ በ1619 አካባቢ ነው። ህጎቹም የሚከተሉት ናቸው።
1. ሁሉም ፕላኔቶች በፀሐይ ዙርያ ይሽከረከራሉ።
2.ፕላኔቶች ወደ ፀሐይ ሲጠጉ በፍጥነት ይሽከረከራሉ።
3.አንድ ፕላኔት በፀሃይ ዙርያ ለመሽከርከር የሚፈጅበት ግዜ ከፀሀይ ባለው ርቀት ይወሰናል።
ይሄንን ህጎች በመንደፍ አለም አሁን ስለ ህዋ ለደረሰችበት ልህቀት የበኩሉን አበርክቶ አልፏል።

አልበርት አንስታይን ለምድራችን ያበረከታቸው በረከቶች

The photoelectric effect ይህ ስለ ብርሀን ጨረሮች የተለየ ባህሪ ያጠናበት እና የኖቤል ሽልማቱን የተቀበለበት ስራው ነው። ይህም እንዴት አትክልቶችና ባትሪዎች የብርሃን ሃይልን ወደ ኤሌክትሪክ የመለወጥ ባህሪ እንደሚኖራቸው የፃፈበት ነበር።

Atom interferometers

"Making the invisible, visible"
ይህ የማይታየውን ለማየት የሚያገለግል theory ነው። ማለትም ቅንጣቶችን በስበት በመታገዝ የተለየ ፍጥነት እንዲኖራቸው ማድረግ ከዛም በተለያዩ ቱቦ ከተጓዙ በኋላ አንድ መስመር ላይ እንዲገናኙ ማድረግ ነው። የተከፋፈሉት ቅንጣቶች አንድ ቦታ ላይ ሲገናኙ ሂደቱ (በተለይም በስበት ምክንያት) የተለያዩ ባህሪ እንዲይዝ ስለሚያደርጋቸው እርስ በርስ በመጠላለፍ (interference) ሌላ ገፅታን ይፈጥራል። ይህ ሁኔታም በአይን የማይታይ ነገሮችን ለማየት ያስችላል።

Making an atomic Blob

ይህ ተመሳሳይ ገፅታ ያላቸውን አተሞች ወደ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በማውረድ ለማቀዝቀዝ የ "Lase beams" ወይም የብርሀን ፎቶኖችን ይጠቀማሉ። ፎቶኖቹ ቅንጣቶችን ወደ 0c (absolute zero) በማድረስ ትልቁን አተም (condensate) እንዲያደርጉ ያደርጋቸዋል።

Brownian Ratchets

እያንዳንዱ ቅንጣት(Particle) በውሀ ላይ የሚኖረው ዝብርቅርቅ እንቅስቃሴ(Random walk) የተለያየ ነው። ምናልባትም እንደ ክብደቱም ወይም እንደ ባህሪው ይወሰን ይሆናል። ይህ ሁኔታም እያንዳንዱ ቅንጣት እንቅስቃሴ አንድ አይነት አቅጣጫ እንዲይዝ የሚያደርገው ሲሆን ሁኔታዎቹም የተለያዩ ቅንጣቶችን ለመለየት ያስችላሉ። ምክንያቱም እያንዳንዱ ቅንጣት በፈሳሽ ውስጥ የሚኖረው እንቅስቃሴ የተለየ ነው።
photo multipliers laser-
master (microwaves amplification through stimulated emission radiation.)
ፎቶ መልቲ ፕላየር የሚባሉት የፎቶ ኤሌክትሪክ ውጤቶች ሲሆኑ በፎቶ ግራፍና ቪዲዮ ካሜራዎች ውስጥ የብርሃን ጨረር (photon) ወደ ኤሌክትሪክ ምልክት (signal) እንዲለወጥና አዲስ ኤሌክትሮኖች እንዲፈጠሩ የሚያደርግ ነው።
አበቃሁ! ...ሰላም!!

ethio SPARK
SOFTWARE DEVELOPMENT

Our Services

Software system development

Mobile application development for IPhone and Android

Desktop application development for Windows, Linux and Mac OS

Website development with an attractive user interface and better user experience

All of our developments are very affordable and customer based. Our goal is your satisfaction in our work.

CONTACT US 0975128309

በ ዳዊት ላቀው

ብቸኝነት ለሚወዱ ሰዎች አስደንጋጭ የጥናት ውጤት

በአለማችን ላይ በርካታ ሰዎች ብቸኝነትን መርጠው በብቸኝነት ሲኖሩ እንዲሁም አንዳንዶች እንደውም ብቸኝነትን በተለየ መንገድ በተለይም ሰው ከሚኖርበት ቦታ በመገለል በጫካ ውስጥ እና ሰው ከሚኖርበት አካባቢ ተገለው፤ ሰዎች ከማይኖሩባቸው ቦታዎች ላይ ለመኖር እና ብቸኝነትን ለማጣጣም የሚፈልጉ እና የሚወዱ በርካቶች እንደሆኑ ይታወቃል። በርካቶች በተለምዶ ብቸኝነትን ሰላም እና ደስታን እንደሚሰጥ እንዲሁም ከብዙ ነገሮች ተቆጥቦ ለመኖር አማራጭ የሌለው መፍትሄ እንደሆነ ሲናገሩ ይስተዋላል ነገር ግን በቅርቡ ታዋቂው መፅሔት ሪደርስ ዳጀስት ሄልዝ አምዱ ላይ ሰፋ ባለ መንገድ ባወጣው መረጃ ላይ እንደጠቀሰው ብቸኝነት በርካታ የጤና ጉዳትን እንደሚያስከትል ባለሙያዎችን እና ጥናቶችን ጠቅሶ ገልፆል።

በተለይም በዚህ ዘገባ ላይ እንደተቀመጠው የዚህ ዘርፍ ባለሙያዎች እንደሚገልፁት ብቸኝነትን ምርጫቸው ያደረጉ እና በብቸኝነት ህይወት ውስጥ ያሉ እንዲሁም ብቸኝነት ጥሩ ነው ብለው ሸንጣቸውን ገትረው ለሚከራከሩ እና ስለብቸኝነት ጠቀሜታ የሚያወሩ እና በዛ ህይወት ውስጥ ያሉ ሰዎች የተሸሸጋቹህበት እና ምርጫቹህ ያደረጋቹህት ብቸኝነት ጉድ ይዞባቹህ መጥቶል ይላል። የጥናት ውጤቱ በዚህም መሰረት ብቸኛ ሰዎች ለበርካታ የጤና እንከኖች ይጋለጣሉ። ከዛም በተቃራኒው ደግም፤ ጓደኞች ያላቸው ሰዎች ከጓደኝነት ህይወት ከሚጠቀሙት ነገር መካከል በተለይም ጓደኛ ያላቸው ሰዎች ከጭንቀት እና ከድብርት ከመሳሰሉ በሽታዎች የዳኑ ናቸው ተብሎል። እንዲሁም የአስተሳሰብ ደረጃቸው እንዳይደክም እና እንዲሁም ለልብ በሽታ እንዳይያዙ ያደርጋል የጓደኝነት ህይወት፤ ይላሉ የዚህ ዘርፍ ተመራማሪዎች።
በጓደኝነት ህይወት ውስጥ ያላቹህ እናንተ ሳትረዶቸው እና ሳታውቆቸው በርካታ ነገሮችን ከጓደኞቻቹህ እየተጠቀማችሁ ነው ይላል ጥናቱ።

በተለይም በዚህ ጥናት ላይ እንደተቀመጠው በአሜሪካን ሀገር ሴንሰስ 2010 እንደተቀመጠው በአሜሪካን ውስጥ በርካታ እድሜያቸው የገፉ ሰዎች በብቸኝነት ህይወት ውስጥ እንዳሉ ተቀምጦል እንዲሁም 47.6 የሚሁኑ ሴቶች እና 27.2 ፐርሰንት የሚሆኑት ወንዶች በብቸኝነት ህይወት ውስጥ እንዳሉ ተጠቅሶል እንዲሁም ከ 10 እስከ 43 ፐርሰንት የሚደርሱ እድሜያቸው ከ65 በላይ የሆኑ ሰዎች በመህበረሰቡ ውስጥ በተለያየ ምክንያት የተገለሉ በመሆናቸው የተነሳ በብቸኝነት ውስጥ ያሉ እንደሆኑ ተቀምጦል። በተጨማሪም ብቸኛ ያለመሆን ከሚሰጣቸው ጥቅሞች መካከል የተስተካከለ አመጋገብ እና የተስተካከለ እንቅልፍ እንዲኖረንም ጭምር የሚያረግ ነው ተብሎል።

በዚሁም ጥናት ላይ እንደተጠቀሰው በሜርላንድ ዩንቨርስቲ በሶሻል ወርክ ትምህርት ቤት ፕሮፌሰር የሆኑት ጂፈሪ ግሪፍ
ሰዎች ለምን ጓደኝነት ለመመስረት እና ከብቸኝነት ለመላቀቅ ዳገት እንደሚሆንባቸው በተለይ ከአስተዳደግ እና ከአኖኖር ጋር በተያያዘ ጓደኝነት ለመጀመር ድክመት የሚሆንባቸው በውስጣቸው በገነቡት የተጎዳ ስሜት መሆኑን ጠቅሰዋል
በተለይ ይህ የማይለወጥ አመለካከት ወይም (stereotypical thinking) ለብቸኝነት ባህሪ መዳበር እና በዛ በሀሪ ውስጥ ተቃኝቶ ለመኖር ከሚነሱ ምክንያቶች ማካከል ግንባር ቀደሙ ነው ይላሉ ፕሮፈሰሩ።

በቦስተን ክሊኒክ ሳይኮሎጂስት የሆነችው እና በሪሌሽን ሺፕ ወይም በጓደኝነት እና በአብሮነት ላይ ስፔሻላይዝድ ያደረገችው ጄና ኮርቲዝ በርካታ የሚሆኑ ሰዎች ለምን ጓደኛ እንዳልኖራቸው እና በብቸኝነት አለም ውስጥ እንደሚኖሩ ስታብራራ በርካቶች ጓደኞች እንዲኖራቸው ይፈልጉና ግን በውስጣቸው ያለው (inferiority) የብቸኝነት ስሜት የተነሳ እራሳቸውን ያገላሉ።

ይህ ስሜት በጣም በርካቶችን ብቻቸውን እንዲሆኑ እና ለድብርት እና ለሌሎችም በርካታ ህመሞች እንዲጋለጡ አድርጎቸዋል ነገር ግን ፍርሀት በተፈጥሮ ማንም ሰው ላይ ያለ ቢሆንም ያንን ለማስወገድ የሚደረግ ጥረት አንድ ሰው ሁሌም ሊተገብረው የሚገባ እና ብቸኝነት የሚያመጣቸውን ማህበረዊ እንከኖች እንዲሁም ያን ተከትሎ ለሚከሰት ህመም ከመጋለጥ በራስ ጥረት እና በባለሙያ በመታገዝ ከብቸኝነት ስሜት በመውጣት በብዙ ነገሮች እንጠቀማለን ይለሉ ባለሙያዋ።
በዶክተር አሌክስ ሊከርማን በሳይኮሎጂ ቱደይ ላይ ጓደኝነት ስላለው የጤና ጥቅም ሲገልፁ በተለይም መህበራዊ ጤናን በይበልጥ እንደሚያግዝ ይገልፃሉ ይህ የጓደኝነት ህይወት ብቸኝነት ከሚሰጠው ደስታ የበለጠ ሰዎች ከራሳቸው እና ከሌሎች ሰዎች ጋር ጤነኛ እና ደስተኛ ግዜያትን እንዲያሳልፉ ከማድረጉም ባለይ ከጓደኞቻቸው የሚያገኟቸው እውቀቶች የስራ እና የህይወት ክህሎቶች በህይወታቸው በርካታ ጠቀሜታዎች ያላቸው ናቸው።

በተጨማሪም (What are the benefits of friendships?) በሚል የጥናት ውጤት ላይም እንደተቀመጠው ጓደኝነት የሚሰጣቸው በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት ከነዚህም ውስጥ ጓደኝነት የበታችነት እና የዝቅተኝነትን ስሜት ያጠፋል፤ጭንቀትን ይቀንሳል ደስታን ይጨምራል፤ በራስ መተማመንን ይጨምራል፤እንዲሁም ጓደኝንት በተፈጥሮም በአደጋም በህይወታችን ከሚገጥሙን በርካታ ችግሮች በቀላሉ እንድንወጣ እና እንድንፅናና ያደርገናል በተለይ በሞት ግዜ፤በፍች ሰአት በንብረት እና በአካል ውድመት እና ጉዳት ወቅት፤ ስራ በሚበላሽበት ሰአት ጓደኝነት ወይም በጓደኝነት ህይወት ውስጥ ከምናገኛቸው ነገሮች ዋነኛዎቹ መፅናናትን እና የመንፈስ ጥንካሬን ያስገኛል

በተለይም በሀገራችን በሀዘን ጊዜ ሀዘንተኛው ከሀዘን እንዲፅናና ጓደኝነት የሚሰጣቸው ጠቀሜታዎች በርካታ ናቸው። በተለይም ሀዘንተኛው ከሀዘኑ እንዲፅናና በጓደኞቹ እና በቤተሰቦቹ አማካኝንት ብቸኛ እንዳይሆን የማህበረሰቡ በባህል ለረጅም ጊዜ ልክ እንደ ልማድ ቢያስቀምጠውም ነገር ግን ይህ ባህል ሰውች ከብቸኝነት ወጥተው በራሳቸው ጥንካሬ እንዲያገኙ እና ጥሩ የሆነ ስነልቦናን እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል። ይህም የጎደኝነት ትልቁ ጠቀሜታ ነው፡ ምክንያቱም ማህበራዊ እና ግላዊ ህይወትን ይበልጥ ጥሩ እና መልካም እንዲሆን ያደርጋል።

እነዚህ ከላይ ያነሳናቸው የጥናት ውጤቶች እና የተለያዩ ባለሙያዎች ሙያዊ ትንታኔ መሰረት ብቸኛ ከሆኑ ሰዎች በርካታ የሆኑ ማህበራዊም እንዲሁም ከዛ ጋር በተያያዘ ለተለያየ በሽታዎች ይጋለጣሉ ነገር ግን ከብቸኝነት ወጥቶ ጥሩ ጓደኝነት መመስረት እና የጓደኝነት ህይወት ውስጥ መኖር ግላዊና ማህበራዊ ህይወትን ከማስተካከሉም በተጨማሪ በህይወት ስኬትን እንድንጎናፀፍ የደርገናል እንደሚሉት የዚህ ዘርፍ ባለሙያዎች ከብቸኝነት አብሮነት እና ጓደኝነት ይሻላል መልክታችን ነው። ሰላም!!

KENDIL Digital Magazine

Contact Us

0912178520
0920019699

300 ሺህ ሰዎችን ይድረሱ!

ምርትና አገልግሎትዎን በቀንዲል ዲጂታል መፅሔት ያስተዋውቁ፡፡ በገቢው ግማሽ የበጎ አድራጎት ስራን ይደግፉ፡፡

ለበለጠ መረጃ (+251) 0912178520 (+251) 0920019699 ይደውሉ!

በዮናስ ሀ/ማርቆስ
(lijyoha@gmail.com)

ሰላም እንደምን ሰነበታችሁ?ቢያነቧቸው ይጠቀሙባቸዋል ብዬ የማስባቸውን መጽሀፍት በዚህ አምድ ስር እጋብዛለሁ።መልካም የንባብ ጊዜ!

በፍቅር ስም

በፍቅር ስም አለማየሁ ህይወትን ባልተለመደ/ በተገለለ የማህበረሰባችን አካል ዐይን እንድናይ ዕድል የሰጠን፤ሌላኛው ድህረ ዘመናዊ ድርሰቱ ነው።...በምናባዊ አለም እውናዊው ህይወት መሐል ያበጀነውን መስመር አጥፍቶ የሁለቱን ዓለሞች ግንኙነት ደግመን እንድንጠይቅ ቆስቁሶን ወደ ትረካው ይሻገራል"ሲል የስነፅሁፍ ተመራማሪው "ቴውድሮስ አጥላው"በመፀሀፉ ጀርባ አስተያየቱን አስፍሯል።
መፅሀፉ በ ሶስት ዋና ዋና ክፍሎችና በ216 ገፆች የተዘጋጀ ሲሆን በ71 ብር ለገበያ ቀርቧል።ደራሲው ከዚህ ቀደም "አጥቢያ" "ወሪሳ" "የብርሀን ፈለጎች" "ቅበላ" እንዲሁም ሌሎች ተወዳጅ ስራዎቹን ለተደራሲያን ማብቃቱ ይታወሳል።

የኢትዮጵያ የአምስት ሺህ አመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ

የኢትዮጺያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢህአዴግ ለመጀመሪያ ጊዜ ለተደራሲያን የበቃው በ 2003 ዓ.ም ሲሆን እስከ 2011ባለው ጊዜ ውስጥ ከ 10ጊዜ በላይ ለህትመት በቅቷል።ይህ መጸሀፍ በሁለት ጥራዝ ለንባብ የበቃ ሲሆን ሁለተኛው ጥራዝ በ2004ዓ.ም ለተደራሲያን ቀርቧል።በጋዜጠኛ ፍስሐ ያዜ የተፃፈ ሲሆን በሁለት ጥራዝ የቀረበ ሆኖ እናገኘዋለን።
የመጀመሪያው ጥራዝ:-ከ ኖኅ እስከ ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ ዘመነ መንግስት ያለውን የሚዳስስ ሆኖ እናገኘዋለን።
ሁለተኛው ጥራዝ:-ከ ልጅ እያሱ እስከ ኢህአዴግ ያለውን ታሪክ ይዳስሳል።የኢትየጵያን የ5ሺ ዓመት ታሪክ በሁለት ጥራዞች አጠናቆ ማቅረብ ቢከብድም በድንቅ የአፃፃፍ ስልት ክሽን አድርጎ አቅርቦልናል።መፀሀፉ መሰረታዊና መካተት አለባቸው ተብሎ የሚታሰቡ የሀገራችንን ታሪኮችና ያልተዳሰሱ ታሪኮቻችን ላይ ጥሩ እውቀትን የሚያስጨብጥ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።
የመጀመሪየው ጥራዝ:-በ 81 ምዕራፎች እና በ463 ገጾች የተቀነበበ ሆኖ በ250ብር ለገበያ ቀርቧል።
ሁለተኛው ጥራዝ:-ካለፈው ጥራዝ በቀጠለ 4ምዕራፎችና በ380 ገጾች ተዘጋጅቶ በ170ብር ለገበያ ቀርቧል::

ግራጫ ቃጭሎች

ለመጀመሪያ ጊዜ በ 1997 ለንባብ የበቃውና በተደጋጋሚ ለህትመት የበቃው የደራሲ አዳም ረታ “ግራጫ ቃጭሎች” እነዲያነቡት ሁለተኛ ግብዣዬ ነው፡፡
“መዝገቡ በዛብህ አይደለም፡የስብእናው ማራኪነትና ሳቢነት ግን የሱን ያህል ነው፡፡ ሰብለ ገነት አይደለችም፤እንጀት ለመብላት ከሆነ ግን በሁለመናዋ ከ ሰብለ አትተናነስም፡፡ ነፋስ መውጫ ከዛ በፊት በስፋት እንደማትታወቀው ማነኩሳ አይደለችም፤ ነገር ግን በ መዝገቡ የተነሳ እንደ ማንኩሳ በልብ ተቀርፆ የማይዳፈን ጉጉት ትፈጥራለች፡፡ አዳም ረታ አዲስ አለማየሁ አይደሉም፤ ይሁን እንጂ በስነፅሁፋቸው ሌላ አዲስ ትውልድ የደረሰበትን የህይወት ምዕራፍ፤ አእምሮው የሚያሰላስለውን፤ ልቡ የሚመኘውን ራዕዩን በመሳል ግን የሚያስደስቱ፤ የአዲስ አለማየሁ ደቀመዝሙር ባይሆኑም የሚኮሩባቸው ውብ የፈጠራ ተውፊት ታማኝ ባለአደራና፤ በዚህም ክብርና ተወዳጅነት ወራሽ ለመሆን የበቁ ደራሲ ናቸው፡፡ ግራጫ ቃጭሎች ፍቅር እስከ መቃብር አይደለም፡ ሊሆን መሞከሩም አይታሰብም፡፡ ግን እንደ ፍቅር እስከ መቃብር የ ኢትዮጵያን ውጥነቅጥና አስገራሚ እውነታ ስዕል አካቷል፡፡ ከገጠር እስከ ዋናዋ ከተማ፤ ከገበሬ እስከ ወፈፌ፤ከምሁር እስከ አስማተኛ፤ከ ወታደር እስከ ቦዘኔ፤ከታሪክ እስከ ተረት፤ከሰቆቃ እስከ ልብ የሚተረትር የደስታ ሳቅና ሁካታ ይጋብዛል፡፡”ሲል “ወርቁ ሻረው”በመጸሀፉ ጀርባ አስተያየቱን አስፍሯል፡፡
መፅሀፉ በ ሁለት ምዕራፎችና በ 446 ገፆች የተቀነበበ ሲሆን በ 120 ብር ለገበያ ቀርቧል ደራሲው ማህሌት፣ አለንጋና ምሳር፣መረቅ፣የስንብት ቀለማት፣እቴሜቴ ሎሚ ሽታ እና ሌሎች ጥራዞችን ለንባብ ማብቃቱ ይታወሳል፡፡



ለውጥ ፈላጊዎች

ለመጀመሪያ ጊዜ በ መጋቢት ወር 2008ዓ.ም ለንባብ የበቃው እና በ ያሲን መሐመድ(ካውንስሊንግ ሳይኮሎጂስት)የተፃፈው ይህ መፅሀፍ በ አምስት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለና በ212ገፆች የተቀነባበረ ሲሆን በ61 ብር ለሀገር ውስጥና ለውጭ አንባቢያን በ25 የአሜሪካ ዶላር ለገበያ ቀርቧል፡፡

የዚህ እትም የመጸሀፍት ግብዣዎቼ ይህን ይመስላሉ በቀጣይ እትም በሌሎች
የመፅሀፍት ግብዣዎች እስክንገናኝ ሰላም!!፡፡
——"ሰላም በምድራችን ላይ ይስፈን"——

በዞስ ካለስ

የሙዚቃ ስልጠና የወሰዱ ፣ወይም ሙዚቃን አዘውትረው ሚሰሙ ሰዎች፣ ከሌሎቹ በተለየ መልኩ ሀሳባቸውን መሰብሰብና ጠንካራ የሰራተኝነት ዝንባሌ እንደሚያዳብሩ ተገለፀ!

ሙዚቃ ማለት ምን ማለት ነው? ሙዚቃ ሚለው ቃል ከግሪክ የመጣ ሲሆን "mousike" ከሚለው ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም "የሙሴ ጥበብ" ሚለውን ትርጉም ይሰጠናል፣ 550 ዓ.ዓ በፊት በግሪክ የሙዚቃ ስልጠና ይሰጥ እንደነበር ጥናቶች አረጋግጠዋል፣ ከ7000 - 6600 ዓ.ዓ በፊትም በቻይና ይጠቀሙበት የነበሩ ብዙ የሙዚቃ እቃዎችና መጫወቻዎች በቻይና ተገኝተዋል። ይሄም ከሰው ልጅ እድገት፣ ለውጥ፣ ታሪክ፣ ባህልና ማህበረሰባዊ ቁርኝት ነጥሎ ሙዚቃን ማየት አይቻልም፣ የሙዚቃ እድገትም ቢሆን አሁን ካለንበት ደረጃ ለመድረ ብዙ ውጣ ውረዶችና እድገቶችን አሳይቶ አሁን ካለንበት ዘርፈ ብዙ ደረጃ ደርሷል፣ ከክላሲካል ሙዚቃ ምት ጀምሮ እስከ ከባድ የሮክ ሚዚቃዎች ድረስ በተለያየ ይዘትና ፍላጎት መሰረት በብዙ ሰዎች ዘንድ ይሰማል፣ ውስጡ ከያዛቸው ጥዕም ዜማና ግጥም በተጨማሪ በዛ ያሉ ረቂቅ ትልሞች ውህድ የሆነው ሙዚቃ፣ ትልቅ የመዝናኛ ኢንዱስትሪ መሆኑን ማንም ሚያውቀዋ ሀቅ ነው፣ አሁን በቅርብ በብዙ መልኩ ሙዚቃ ላይ እየተደረጉ ያሉ ምርምሮች ለዚ ማሳያ ናቸው፣ አሁን በቅርብ ሄሊዮን ጆርናል ላይ በወጣው አዲስ ጥናት ይፋ እንዳሆነው፣ የሙዚቃ ስልጠና የወሰዱ ወይም ደግሞ አዘውትረው ሙዚቃ ሚሰሙ ሰዎች ከሌሎች ካልሰለጠኑት ወይም አዘውትረው ከማይሰሙት ሰዎች የበለጠ ሀሳባቸውን መሰብሰብ እንደሚችሉ ጥናቱ አመልክቷል።

አጥኚዎቹ እንደሚሉት ከሆነ በዋነኝነት የምርመራቸው ጥናት ማስኬድ የፈለጉት የአዕምሮ ትኩረት ማድረግ ላይ ሙዚቃ ሚያመጣውን ተፅኖ ለማወቅ ቢሆንም፣ ከሱጋ በተያያዘ ሌሎች ሙዚቃ ሚያመጣውን ገፀ በረከቶች አብስረዋል፣ እንደ ዶ/ር ፓውሎ ባራዛ(የቺሉ ዩኒቨርሲቲ፣ ሰንቲያጎ፣ የምርምር አባል) ገለፃ ከሆነ የሙዚቃ ስልጠናም ሆነ የመስማት ክህሎታቸው በጨመር ቁጥር የአዕምሮ ንቃተ ህሊና መጨመሩ አይቀሬ መሆኑን ተናግረዋል፣ ትኩረት የማድረግ አካሄድ በሶስት አናቶሚካል የመዋቅሮች አውታር ኒውሮንን በማካለል የተዋቀረ ሲሆን እነዚህም የማስጠንቀቂያ አውታሮች፣ ጠቋሚ አውታሮችና የመከላከልና የማስተካከል አውታሮች ናቸው። የማስጠንቀቂያ አውታሮች የድርጊቶችን ሂደት በጥንቅቄ ይመለከታል፣ ጠቋሚ አውታሮች ምንፈልገውን መረጃ ማቅረብና ወደ ምንፈልገው አቅጣጫ መጠቆም ስራቸው ሲሆን፣ የመከላከልና የማስተካከል አውታሮች ደግሞ ማይጠቅሙ፣ ሚረብሹትንና ጣልቃ ሚገቡ ድርጊቶችን መከላከልና ማስቆም ነው።



አጥኚዎቹ እንደሚሉት ከሆነም በማስጠንቀቂያና በመጠቆሚያ አውታሮች መሀል ያሉ ስርአተ ሂደቶች ሙዚቃ በሚያዘወትሩት ላይ ፈጣንና የተስተካከለ እንደሆነ ገለፀዋል።

ጥናት ተደርጎባቸው በተመዘገበ መረጃ መሰረት 18 ሚሆኑ የፒያኖ ልሂቃንና 18 ሙዚቃ በማያዘወትሩ ወይም ጭራሹኑ የማይሰሙ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና ተመራቂ ተማሪዎች ላይ ጥናት ተደርጎ፣ በሚመልሱት ፈጣን ግብረ መልስ ላይ በመነሳት የተለያየ ፈጣን የስዕል ቅንብር በማሳየት በተደረገው የመለያ ጥናት፣ የማስጠንቀቂያ፣ ጠቋሚና የመከላከልና የማስተካከል አውታሮች በቅደመ ተከተል ይሄን ደረጃ አግኝተዋል፣ በዚህም 43.84 ሚሊሰከንድ(Ms), 43.70 Ms እና 53.83 Ms ነጥብ ሙዚቃ በሚሰሙት በኩል ሲገኝ። ሙዚቃ በማይሰሙት 41.98, 51.56 እና 87.19 ነጥብ አምጥተዋል። ትልቅ ነጥብ ያመጡት ዝቅተኛ ትኩረት የማድረግ ብቃት ሲኖራቸው፣ ትንሽ ነጥብ ያላቸው፣ በትንሽ ግዜ ውስጥ ሀሳባቸውን በመሰብሰብ ትኩረት ለሚያስፈልገው ነገር ዝግጁ መሆን ሚችሉ ሰዎች መሆናቸውን ጥናቱ አስነብቧል።

ቀደምት አጥኚዎች እንደሚሉት ከሆነ ፣ሙዚቃን ማዘውተር ትኩረት ከማድረግና ሀሰብን ከማሰባሰብ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን፣ የማስተወስና ንቁ አዕምሮ እንዲኖርና እንደሚያግዝ ገልፀዋል። ሌላ ከሙዚቃ ጋ በተያያዘ ጥናት፣ የዳብስቴፑ የኤሌክትሮኒክስ ሙዚቃ አቀንቃኙ ስክሪሌክስ፣ ሚለቃቸው ዘፈኖች ከቢንቢ የወባ ትንኝ ንክሻ እንደሚከላከል ተገልፆል፣ የኤሌክትሮኒክስ ሙዚቃዎች እንዴት የወባ ትንኝ ሊከላከሉ ይችላሉ ሚለው፣ የሁለችንም ጥየቄ መሆኑ አያጠያይቅም፣ አጥኚዎቹ እንደሚሉት፣ የግራሚ ምርጥ አልበም ተሸላሚ የሆነው የስክሪሌክስ ዘፈኖች፣ በትልቅና በትንሽ ፍሪኪዌንሲ የሚየጫውት ሲሆን፣ በዝቅተኛው ምት ሚለቀው የሙዚቃው ፍሪኪዌንሲ፣ የወባ ትንኝን ስረአተ አፈጣጠር ግስጋሴ፣ እንቁላሎቹ ሚፈጠሩበትን ሂደት በማዛባት ያበላሸዋል፣ ትንኞቹን በማወክብም፣ የሰውን ደም የመምጠጥ እንቅስቃሴ የተገደበ ያደርገዋል ።

ምስጋና

ከሁሉ አስቀድመን በመፅሔታችን መከናወንን ለሰጠን በብዙ ላገዘን እና ለረዳን፡ ጥበቃውን፡ምህረቱንና ቸርነቱን ላበዛልን፡ ሀያሉ እግዚብሔር ምስጋና ይድረሰው። ቀንዲል ዲጂታል መፅሔትን ስናዘጋጅ ሞራል የሰጡንን ያበረታቱንን በሙሉ ምስጋናችን በያሉበት ይድረሳቸው። እንዲሁም መፅሔታችንን ይበልጥ ዲጂታላይዝ ለማድረግ በምናደርገው እንቅስቃሴ ውድ ጊዜያቸውን እና እውቀታቸውን በነፃ ሰውተው የቀንዲል መፅሔት ሞባይል መተግበርያ ለሰሩልን የኢትዮ ስፓርክ ባለቤት ሄኖክ መንግስቱ ምስጋናችን የላቀ ነው። እንዲሁም መፅሔታችንን በተወዳጅ የቴሌግራም ቻናላቸው ላይ የለቀቁልንን TIKVAH-ETH፡ ግጥም ብቻ፡ዞዳይክና ከመፅሐፍት አለም ቻናሎች ምስገናችን ይድረሳቸው። እናንተም ውድ አንባቢዎች የመጀመርያ እና ሁለተኛ ስራችንን ተመልክታች ለላካችሁልን ገንቢና መልካም አስተያየት እጅግ አድርገን እያመሰገንን አሁንም አስተያየታችሁ አይለየን እንላለን።

ሰላማችሁ ይብዛ!!

Telegram | @KendilM
FaceBook | KendilM